# የሥነ-ጥበብና ሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት

# 1ኛ ክፍል

## ምዕራፍ አንድ፡- በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች *(61 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን ቀለም፣ ቅርፅ፣ ድምፅ፣ እንቅስቃሴ በማስተዋል በተግባር ሠርተው ያሳያሉ።
- በጨዋታና በተለያዩ ተግባራዊ ሥራዎች ይሳተፋሉ፣
- በጨዋታዎችና በተግባራዊ ሥራዎች በመሳተፍ ሕጐችን ያከብራሉ፣
- ምስላቸውን ድምጻቸውንና እንቅስቃሴያቸውን አስመስለው በመሥራት የሙከራ ችሎታቸውን ያሳያሉ፣
- ስለቤተሰብ አባላትና ኋላፊነት የተረዱትን ይገልፃሉ፣

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች፡-*<br>• ከ1-2 የቤተሰብ አባላትን፣ ኋላፊነትና የሥራ ድርሻ ይገልፃሉ፣<br>• ከመታዘዝ፣ ማክበር፣ መረዳደት እንዲሁም ከቤተሰብ አባላት የሥራ ድርሻ ጋር የተያያዘ ቀላል መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br>• ከመዝሙሩ ጋር የሚሄዱ እንቅስቃሴዎችን ሠርተው ያሳያሉ፣ | **1.1 ቤተሰብ** *(20 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.1.1 የቤተሰብ አባላት እናት፣ አባት፣ ወንድም እህት<br>• ስለ ቤተሰብ አባላት መዘመር፣ | • ከተማሪዎች ልምድ በመነሳት በቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በየተራ እንዲዘረዝሩ መጠየቅና ሁሉም በመመለስ እንዲሳተፉ ማበረታታት።<br>• በቤት ውስጥ ከሚገኙ ነገሮች በቤተሰብ አባላት ላይ ትኩረት በመስጠት የእናት አባት ወንድም እህትን ኃላፊነታቸውን፣ የሥራ ድርሻቸውን ወዘተ... የተመለከተ የሚያውቁትን እንዲገልፁ በማድረግ ማወያየት። በተለይም ለእናትና አባት መስጠት ስለሚገባው ክብር እናትና አባትን መታዘዝ፣ ከወንድምና እህት ጋር መፈቃቀር መረዳዳት፣ መከባበር እንደሚገባ ወዘተ.. የሚገልጹ መዝሙሮችን መጀመሪያ በካሴት ማሰማት፣ ከዚያም በመዝሙሩ ውስጥ የተላለፉትን መልዕክቶች ምን ምን እንደሆኑ ካደመጡ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት፣<br>• በመቀጠል የመዝሙሩን ግጥሞች ማስጠናትና መዝሙሩን ከዜማው ጋር እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• በቤጨረሻም ከመዝሙሩ ጋር ተማሪዎችን የቤተሰብ አባሎቻቸውን ዋና ዋና ተግባራት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ ድምፃቸውን አነጋገራቸውን ቅርፃቸውን አስመስለው እንዲያሳዩ ማበረታታት፣ |
| • የቤተሰባቸውን ተግባርና ድምፅ አስመስለው በመሥራት ከ1-2 የድምፅ ልዩነቶችን ይገልፃሉ፣ | 1.1.2 የቤተሰብ አባላትን ድምፅ ማውጣት | • የቤተሰብ አባላት ተግባራትን አስመስለው እንዲሠሩ ማበረታታት እንቅስቃሴያቸውን ድምፃቸውን ሲቆጡ፣ ሲመክሩ፣ እንግዳ ሲቀበሉ፣ ሲሠሩ፣ ሲበሉና ሲጋብዙ ወዘተ... እንዴት እንደሆነ በመጠየቅ አስመስሎ የመሥራት ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ፣ |
| • የቤተሰባቸውን እንቅስቃሴ አመስለው | 1.1.3 እንቅስቃሴ | • ተማሪዎች የቤተሰባቸውን አባላት ምስሎች በሥዕል |

| ***የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ*** | ***ይዘት*** | ***የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች*** |
|---|---|---|
| ይሠራሉ፣ | | እንዲሠሩ ማድረግ፣ የሠሯቸው ስዕሎች ለክፍል ተማሪዎች እንዲያስረዱ ማድረግ፣ |
| • የቤተሰብ አባላትን ምስል በንድፍና በቅርጽ ለመሥራት በሚያደርጉት ልምምድ ሀሣባቸውን በንድፍ ይገልፃሉ፣ | 1.1.4 የቤተሰብ አባላትን ምስል በንድፍና በቅርፅ መሥራት | • ከሠሯቸው ስዕሎች ውስጥ የተሻለውን በጋራ እንዲመትጡ ማድረግ፣<br>• በመቀጠል የእናት፣ የአባትና የልጆችን የሚያሳዩ ስዕሎችን ፖስተሮችንና ፎቶግራፎችን በማሳየት አስመስለው እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የእናትና የአባት ሞዴሎችን በጭቃ፣ በወረቀት ጭቃ ወዘተ… እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ስለሠሩት ሥራ ገለፃ እንዲያደርጉት መጠየቅ፣<br>• የተሻለ ሥራዎች በመምረጥና በክፍሉ ተማሪዎች በሚያዩበት ቦታ በሞዴልነት ማስቀመጥ፣ |
| የቤተሰብ አባላትን ልዩ ልዩ ተግባራት አስመስለው ይጫወታሉ፣ | 1.1.5 ስለቤተሰብ አባላት ተግባር በድራማ መጫወት | • ልዩ ልዩ እቃዎችና አልባሳትን እንዲያመጡና የአባት፣ የእናትና የልጆችን ገፀ ባህሪያት በመወከል ድራማ እንዲሰሩ ማድረግ፣ |
| • ስለ ቤት እንስሳት የሚገልፁ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br><br>• ከዜማው ጋር የሚቀናጁ እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ፣ | **1.2 በቤት ውስጥ የሚገኙ የቤት እንስሳት**<br>*(20 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.2.1 *መዝሙር* /ስለቤት እንስሳት/<br><br>1.2.2 *ድምፅ፣ እንቅስቃሴና ምስልን አስመስሎ መሥራት፣* | • የቤት እንስሳት የተለያዩ መሆናቸውንና የእነዚህን እንስሳት ጠቀሜታ፣<br>• ለእነዚህ እንስሳት መደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ እንዲገልፁ መጠየቅ፣<br>• የእንስሳቱን ድምፅና እንቅስቃሴ አስመስለው እንዲሰሩ ማድረግ፣<br>• ለማነቃቂያ የድመትና የውሻ ምስሎችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ፖስተር ወይም ፎቶራፍ ማሳየትና አስመስለው በንድፍ እንዲሠሩ ቀለማቸውንም እንዲቀቡ ማድረግ፣<br>• ስለሠሯቸው ምስሎችም እያንዳንዳቸው ገለፃ እንዲያደረጉ መጠየቅ፣<br>• ከሥዕሎቹ መካከል የተሻሉትን መምረጥና ለበለጠ ሥራ እንዲያሰቡ ማድረግ፣<br>• በተመሣሣይ ሁኔታ ሌሎች በቤታቸው የሚገኙ እንስሳትን በንድፍና በቅርፅ እንዲሠሩ፣ ንድፉን ተስማሚ ቀለም ቅብ እንዲቀቡት ማድረግ፣<br>• የተሻሉትን አወዳድሮ መምረጥ በሚታይ ቦታ መለጠፍ ማስቀመጥ፣<br>• ስለቤት እንስሳት የሚያውቋቸው ግጥሞችን ካሉ |

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| | | እንዲያነባቸው ማድረግ፣<br>• ስለቤት እንስሳት የተዘጋጀውን መዝሙር ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ የመዝሙሩ ግጥሞች ስለምን እንደሚገልጹ እንዲያብራሩ ማድረግ፣<br>• መዝሙሩን እንደገና ማስማትና እንዲዘምሩ ማበረታታት፣<br>• መዝሙሩን በመከፋፈል እንዲለማመዱት ማድረግ፣<br>• ከመዝሙሩ ዜማ ጋር የሚሄዱ እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት እንዲለማመዱና እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • በአካባቢያቸው ያሉ ቁሳቁሶችን ተጠቅመው ለእንቅስቃሴ መሠሪያ የሚያገለግሉ ኳሶችንና ገመዶችን ያዘጋጃሉ፣<br>• በአካባቢያቸው ያሉ እንደ ቅጠላ ቅጠል፣ ከሰል፣ አፈር ወዘተ.. ነገሮችን በመጠቀም የተለያዩ ቀለማትን ያዘጋጃሉ፣<br>• የተለያዩ ቁሳቁሶችን ተጠቅመው ቅረፃርቅፆችን ይሠራሉ፣ | **1.3 ከአካባቢን የሚገኙ ነገሮችን መጠቀም**<br>*(21 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.3.1 ለኤስቴቲክስ መሣሪያዎች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ማዘጋጀት | • ከተማሪዎች ልምድ በመነሳት በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ እና ከምን እንደሰሩ መጠየቅ፣<br>• ለመጫወቻም ሆነ ለመማሪያ የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ከምን ከምን እንደተሰሩ መጠየቅ፣<br>• በመቀጠልም በአካባቢያቸው ባሉ ነገሮች በወረቀቶች በላስቲክና ቅጠላቅጠሎች ምን ዓይነት ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንደሚቻል መጠየቅ፣<br>• ከዚህም በመነሳት ከወረቀትና ላስቲክ ኳሶች ከቅጠላ ቅጠሎች ቀለማት እንዲሁም ከተለያዩ ነገሮች ገመድ ቅርፃ ቅርፅ እንዲያዘጋጁ ማድረግና በሠሯቸውም ነገሮች እንዲጠቀሙበት ማበረታታት፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ሥዕሎች
- ገመዶች
- ቅርፃ ቅርፆች
- መዝሙር የተቀረፀባቸው ካሴቶች
- ቴፕሪኮርደር
- ቀለማትን ለማዘጋጀት የሚጠቅሙ በአካባቢው  የሚገኙ ቁሣቁሶች/የተለያዩ ቀለም ያላቸው አፈሮች፣ቅጠላ ቅጠሎች ከሠል ወዘተ…/
- ላስቲኮችና ቁርጥራጭ ጨርቆች

## ክትትልና ግምገማ፡-

- የቤተሰብ አባላትንና የኃላፊነታቸው እንዲገልፁ መጠየቅ፣
- ስለቤተሰብ አባላትና የቤት እንስሳት ያስተዋሉትን በንድፍ በቅርፅ በእንቅስቃሴና በድምፅ ለመግለፅ የሚያደርጉትን ተሣትፎ በምልከታ መከታተል፣
- በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን ተጠቅመው የተለያዩ ነገሮችን ለመጫወቻና ለመሥሪያ ማዘጋጀታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ድምፆችን፣ እንቅስቃሴዎችን አስመስለው መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በየርዕሱ የተሰጧቸው መዝሙሮችን ግጥምና ዜማቸውን አዋህደው በትክክል መዘመራቸውን መከታተል፣

## ምዕራፍ ሁለት፡- ባህልና ቅርስ *(40 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** *ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-*

- በአካባቢው የሚዘወተሩ የልጆች ጨዋታዎችን ምን መቼና እንዴት መጫወት እንዳለባቸው ይገልፃሉ፣
- የልጆች ጨዋታዎችን በመገንዘብ ይጫወታሉ፣
- በቤት ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቁሳቁሶችን አገልግሎት በመገንዘብ ይጠቀማሉ።
- ባህላዊ ዘፈኖችዎችን ይጫወታሉ፣

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• በአካባቢው የሚዘወተሩ የልጆች ጨዋታ ዓይነቶችን ከ2-3 ይዘረዝራሉ፣<br>• ምን ጨዋታ በምን ወቅት መጫወት እንደሚገባ ይገልፃሉ፣<br>• በአካባቢው የሚዘወተሩ የልጆች ጨዋታዎችን በህብረት ይጫወታሉ፣<br>• ባህላዊ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፣<br>• ከባህላዊ ዘፈኖች ጋር የሚሄዱ እንቅስቃሴዎችና ጭፈራዎችን ከሙዚቃ ጋር በማቀናጀት ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• የልጆች ጨዋታዎችን በራሳቸው መንገድ በንድፍ ይገልፃሉ፣ | **2.1 የልጆች ጨዋታዎች** *(15 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.1.1 በአካባቢ የሚዘወተሩ የልጆች ጨዋታዎች<br>2.1.2 በአካባቢ የሚዘወተሩ የልጆች ጨዋታዎች ንድፍ | • የሚያውቋቸውን የልጆች ጨዋታዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣ የዘረዘሯቸውን ጨዋታዎች ለጓደኞቻቸው በመጫወት እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• የተመረጡ የተለያዩ የልጆች ጨዋታዎችን በቡድን በመክፈል እንዲጫወቱ ት ማድረግ፣<br>• የተወሰኑ ተማሪዎች ተራ በተራ ከእነዚህ ጨዋታዎች መካከል የተመረጡትን ከሙዚቃ መሣሪያ ጋር በማቀናጀት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ጨዋታዎቹን እንደየዖታው ማበረታታት<br>• ከተሠሩት ጨዋታዎች ውስጥ የመረጡትን በራሳቸው መንገድ በንድፍ እንዲሠሩ ማበረታታትና ስለሠሩት ሥራ ስለአሠራሩ እንዲገልፁ ማድረግ፣ |
| • በቤት ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ባህላዊ ቁሣቁሶቹን እንዴት በጥንቃቄ መያዝ እንደሚገባ ይገልፃሉ፣<br>• ከ2-3 ባህላዊ አልባሳትን ይዘረዝራሉ፣<br>• በራሳቸው መንገድ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችንና አልባሳትን በራሣቸው መንገድ በንድፍ ይሠራሉ፣ | **2.2 በቤት ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቁሳቁሶች***(15 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.2.1 የቤት ውስጥ መገልገያ ባህላዊ ቁሣቁሶች<br>2.2.2 ባህላዊ አልባሳት | • በቤት ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቁሣቁሶችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• ስለአሠራራቸው፣ ጠቀሜታቸውና አጠባበቃቸው በቡድን ተወያይተው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣<br>• የተለያዩ ባህላዊ ቁሣቁሶችን የሚያሣዩ ሥዕሎችን በማሣየት ቤታቸው ውስጥ የትኛው እንዳለ እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>• እነዚህንም በንድፍ አስመስለው እንዲሰሩ ማድረግ፣<br>• ቀለማትን አዘጋጅተው በንድፍ የሠሩትን እንዲያስውቡ ዕርሰ በርስም እንዲወዳደሩ ማድረግ፣<br>• ባህላዊ አልባሳትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ |

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| | | • የባህላዊ አልባሳትን ጠቀሜታ አያያዝ እንዲገልጹ ማድረግ፣<br>• ባህላዊ አልባሳትን ባንድፍ እንዲሠሩ ማበረታታት፣<br>• ከሥራዎች መካከል በተሻለ ሁኔታ የተሰራውን እንዲመርጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ |
| • የልጆች ባህላዊ ዘፈኖችና ከ2-3 ጭፈራዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በባህላዊ ዘፈኖች ጭፈራዎች ይሳተፋሉ፣<br>• የባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን እንቅስቃሴ በራሳቸው መንገድ በንድፍ ሠርተው ያሣያሉ፣ | **2.3 ባህላዊ ዘፈኖች እና ጭፈራዎች**<br>*(10 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.3.1 ባህላዊ ጨዋታዎችና ጭፈራዎች | • የሚያውቁአቸውን ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን እንዲዘረዝሩና እንዲጫወቱ መጠየቅ፣<br>• የመረጡትን ባህላዊ ዘፈኖችን በቡድን እንዲጫወቱ ማድረግ፣<br>• ባህላዊ ጭፈራዎችን በንድፍ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን በተሻለ ሁኔታ የሚጫወቱትን በመለየት ለሌሎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችና አልባሳት
- ባህላዊ ቁሳቁሶች
- ባህላዊ አልባሳት
- ሥዕል

## ክትትልና ግምገማ፡-

- የልጆች ጨዋታዎች ምን ምን እንደሆኑ መቼና እንዴት መጫወት እንደሚቻል እንዲያስረዱ መጠየቅ፣
- የልጆች ጨዋታዎችን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ ቁሳቁሶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣
- ከባህላዊ ዘፈኖች ጋር የሚሄዱ እንቅስቃሴዎችን መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የባህላዊ ዘፈኖች ጭፈራ እንቅስቃሴን በንድፉ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ምዕራፍ ሦስት፡- ጥንቃቄና ደህንነት *(21 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በደረጃቸው የግል ንጽህና ለመጠበቅ ፍላጐት በማሳየት የግል ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ፣
- ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ሀሳባቸውን በመዝሙርና በሥዕል ይገልፃሉ፣
- መንገድና ወንዝ በሚቋረበት ጊዜ መደረግ የሚገባውን ጥንቃቄና ደህንነት ተገንዝበው ይጠነቀቃሉ፣
- በፍጥነት አቅጣጫ የመቀየርን፣ የሰውነትን እንቅስቃሴ የመቆጣጠር መሠረታዊ ክሂሎትን በተግባር ሠርተው ያሳያሉ፣
- ኤች አይቪ ኤድስ ምንነትና መከላከያ ዘዴዎችን ይገልፃሉ፣
- ከርዕሶች ጋር ተያይዘው በሚለማመዷቸው እንቅስቃሴዎች አማካይነት የጊዜ የርቀትና የቦታ ግንዛቤያቸውን በመረዳት ተግባራዊ ያደርጋሉ፣

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች፡-*<br>• ከግል ንጽህና ጋር ተያያዙ መዝሙሮች ይዘምራሉ፣<br>• ስለግል ንጽህና ጥቅም 2-3 ይገልፃሉ፣<br>• ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ሀሳባቸውን በመዝሙርና ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ሠርተው ያሳያሉ፣ | **3.1 የግል ንጽህና አጠባበቅ**<br>*(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.1.1 መዝሙር፡- ስለግል ንጽህና | ተማሪዎች ስለግል ንጽሕና አስፈላጊነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ መጠየቅ፣<br>• የግል ንጽህናን ባለመጠበቅ የሚደርሱ ጉዳቶችን የግል ንፅህናን የመጠበቂያ ዘዴዎች ላይ በማወያየት ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፣<br>• የግል ንጽህናን የመጠበቅ አስፈላጊነት ንጽሕናን ባለመጠበቅ የሚደርሱ ችግሮችን የግል ንጽህናን የመጠበቂያ ዘዴዎች ጋር የተገናኙ መዝሙሮችን በመዝሙር የማስተማር ቅደም ተከተል መሠረት ማስተማር፣ |
| • የግል ንጽህና መጠበቅን የሚገልፁ ሀሳቦችን በንድፍ ሠርተው ያሣያሉ፣ | 3.1.2 በንድፍ አስመስሎ መሥራት፣ | • የግል ንጽህና አጠባበቅን የሚያሣይ የተለያዩ ሥዕሎችን በፖስተሮች መልክ ማዘጋጀትና እንዲጐበኙት ማድረግ፣<br>• የግል ንጽህናን እንዴት በምን መልክና መቼ መጠበቅ እንደሚገባ ሀሣብ እንዲጨብጡ ጥያቄዎችን ማቅረብና ማወያየት፣<br>• በቂ ሀሣብ የጨበጡ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ የግል ንጽህና መጠበቅን የተመለከቱ ርዕሶችን ማዘጋጀትና በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሀሣባቸውን የሚገልፅ የንድፍ ሥራ በፈለጉት መልክ እንዲያቀርቡ የፕሮጀክት ሥራ መስጠት፣<br>• የሁሉም ተማሪዎች ሥራ ተጠናቆ ሲቀርብ ማወዳደርና የተሻሉበትን ራሣቸው ተማሪዎች እንዲመርጡ ማድረግ፣<br>• የተመረጡትን ሥራዎች በሚታይ ቦታ መለጠፍና በሌሎች ማስጐብኘት፣ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • ወድቀው የሚገኙ አንዳንድ ነገሮች፣ እሳት፣ የፈላውኃ፣ ኤሌክትሪክ የሚያስከትሉትን ጉዳት ከ2-3 ይገልፃሉ፣<br>• እነዚህ ነገሮች ጉዳት እንዳያደርሱ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በመዝሙር፣ በንድፍና በእንቀስቃሴ ይገልፃሉ፣ | **3.2 ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች መጠንቀቅ** *(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.2.1 ወድቀው ከሚገኙ ነገሮች፣ ከእሳት፣ ከፈላ ውኃ፣ ከኤሌክትሪክ ወዘተ... መጠንቀቅ፣<br>3.2.2 መዝሙር<br>3.2.3 በንድፍ አስመስሎ መሥራት | • ስለጉዳዩ መጠነኛ ገለፃ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲያከፍሉ ማድረግ፣<br>ለምሳሌ፡-<br>ሀ/ ወድቀው ከሚገኙ ነገሮች አደጋ የደረሰበት ሰውን፣<br>ለ/ እሳት ያደረሰውን ጉዳት ቤት የተቃጠለበት፣ በእሳት የተቃጠለ ሰውን፣<br>ሐ/ የፈላ ውኃ ያቃጠለውን ሰው<br>መ/ በኤሌክትሪ የተያዘ ሰው ወዘተ<br>- ከዚህ ጋር የተያያዙ ፖስተሮች ለምሳሌ እሳት ያቀጠለው ልጅ፣ የፈላ ውኃ የፈሰሰበት በጅ ማሳየትና ተማሪዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣<br>- መደረግ ያለበትን ጥንቃቄም እንዲወያዩበት ማድረግ፣<br>- መዝሙሮችን ተስማሚ የማስተማር ዘዴ ተጠቅሞ ማዘመር፣<br>- መዝሙሩን በደንብ ካጠኑ በኋላ ከተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር እንዲያያዝሉት ማድረግ፣<br>- በራሳቸው መንገድ በጉዳዩ ላይ በንድፍ አስመስለው እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>- የሠሩትን ሥራዎች ለተማሪዎች እንዲያሳዩና አሠራሩንም እንዲገልፁ ማድርግ፣ |
| • የኤች አይ ቪ ኤድስን ምንነት መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን መዝሙሮች በመዘመር ይገልፃሉ፣<br>• ቀላል እንቅስቃሴዎችን ከመዝሙሮቹ ጋር በማቀናጀት ይሠራሉ፣<br>• ስለኤች አይቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች መከላከያ ዘዴዎች የሚገልፁ ንድፎች ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• የኤች አይቪ/ ኤድስን አስከፊነትና የመተላለፊያ መንገዶችን በተመለከተ ያላቸውን ሀሣብ በንድፍ ሠርተው ያሳያሉ፣ | **3.3 ኤች አይቪ/ኤድስ/7 ክፍለ ጊዜ/**<br>3.3.1 የኤች አየቪ/ኤድስን ምንነት<br>3.3.2 መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን<br>3.3.3 መዝሙር<br>3.3.4 በንድፍ አስመስሎ መሥራት | • ተማሪዎች ከሚያውቁት ነገር ለመነሳትና ለማነቃቂያ እንዲሆን ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ፣<br>- ኤች አይ ቪ ኤድስ ምንድነው?<br>- ኤች አይ ቪ ኤድስ እንዴት ይተላለፋል?<br>- ኤች አይ ቪ ኤድስ እንዴት መከላከል ይቻላል?<br>• በጥያቄዎቹ ላይ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ሀሣባቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት፣<br>• የኤች አይ ቪ ኤድስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች የሚያሳዩ ፖስተሮችን ፎቶግራፎችንና ስሥዕሎችን |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | በማሳየት ስለምንነቱ ማወያየት፣<br>• ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ የተዘፈኑ ዘፈኖችን በቴኘ ማሰማት ዘፈኑ ስለምን እንደሆነ መጠየቅ አብረው እንዲዘፍኑ ማበረታታት፣<br>• ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ምንነት መተላለፊያ መንገዶችና መከላከያ ዘዴዎች የሚገልፀውን መዝሙር ማስተማር፣<br>• መዝሙሩን በጥሩ ሁኔታ የሚዘምሩ ተማሪዎችን ከሁለተኛ ወይም ከሦስተኛ ክፍል መጋበዝ፣<br>• በኤች አይ ቪ ኤድስ ላይ የተመሠረቱ አጫጭር ትረካዎችን መንገርና በትረካው ውስጥ የተገለፁ ገፀ-ባህሪያት በመወከል ድራማ እንዲሠሩ ማድረግ።<br>• አስቀድመው ከሚያውቁት በመነሳት በመሰላቸው መልክ የኤች አይ ቪ ኤድስ መተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎችን የሚያሳዩ ሥዕ ሎችን በንድፍ እንዲሠሩ መጠየቅ፣<br>• ስለሠሩት ሥራ እያንዳንዳቸው ገለፃ እንዲያደርጉ እድል መስጠት፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ፖስተሮች

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ስለግል ንጽህና ጥቅም እንዲገልፁ መጠየቅ፣
- ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች እንዴት እንደሚጠነቀቁ እንዲገልናፁ መጠየቅ፣
- የኤች አይቪ ኤድስ ምንነትንና መተላለፊያውን መንገድ እንዲገልፁ መጠየቅ፣
- ወድቀው በሚገኙ አንዳንድ ነገሮች፣ እሳት የፈላ ውኃ፣ ኤሌክትሪክ የሚያስከትለውን ጉዳት መወሰድ የሚገባውን ጥንቃቄ ማወቃቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ፣
- መዝሙሩን ከእንቅሰቃሴው ጋር በትክክል መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

**ምዕራፍ አራት፡- የሰውነት ክፍሎች ተግባራት** *(82 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የአዕምሮና ሰውነት ቅንጅት ችሎታቸውን በማዳበር በተግባር የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ሠርተው ያሳያሉ፣
- የቦታ የጊዜና የኃይል አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን በተግባር ሠርተው ያሳያሉ፣
- ለሚሰሙት ምት ተገቢውን የተቀናጀ የእንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ፣
- በእንቅስቃሴም ሆነ አንድ ቦታ ሆነው ሚዛን የመጠበቅ መሠረታዊ እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ፣

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች በዓይነት የሚመሳሰሉ ከ4-5 ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች አንድ ዓይነት ቀለም ያላቸው ከ5-6 ነገሮችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች በቅርጽ የሚመሳሰሉ ከ4-5 ነገሮችን ይዘረዝራሉ፣ | **4.1 በእጅ የሚከናወኑ ተግባራት**<br>*(35 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.1.1 ነገሮችን በአይነት በቀለምና በቅርፅ መለየት<br>4.1.2 ንድፍ | • የዕለቱን ትምህርት ከመጀመር አስቀድሞ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>• በመቀጠል በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ቀለም ቅርጽና መጠናቸውን እንዲናገሩ እድል መስጠት፣<br>• ተመሳሳይ ቀለም ቅርጽ መጠን አካሄድ ያላቸውን እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>• ቀላል ጉዳት የማያስከትሉ ነገሮችን ምሳሌ ቆርኪ የዛፍ ፍሬዎች፣ የደረቁ ቅጠላቅጠል ጠጠሮች ወዘተ… የመሳሰሉትን ወደ ክፍል ይዘው እንዲመጡ በማድረግ በዓይነት በቅርጽ በቀለም በመጠን ወዘተ… መለየትን እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• ያልገባቸው እንዲጠይቁ ማበረታታት፣ |
| • በተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች ምት የአርምጃ እንቅስቃሴ ይሠራሉ፣ | **4.2 እጅና እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራት** *(47 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.2.1 የእርምጃ ምት | • የክፍሉን ተማሪዎች ተወዳጅ የሆነ ለእንቅስቃሴው ምቹ የሆነ ዘፈን በካሴት ማሰማትና ነፃ ሆነው ከዜማው ጋር እንዲያጨበጭቡ፣ በእግራቸው መሬት በመምታት ድምፅ እንዲፈጥሩ፣ በቦታ ላይ እንዲሄዱ፣ በእግራቸው ጣት እንዲሄዱ፣ እጃቸውን ከራስ በላይ በማንሳት እንዲያወዛውዙ ወዘተ.. ማድረግ፣<br>• የክፍሉን ተማሪዎች በሁለት መክፈልና አንደኛው ቡድን ለእርምጃ ተሰማሚ የሆነውን ባህላዊ ዘፈን እንዲጫወቱ ማድረግ፣ ሌላኛው የቡድን አባላት በጭጨባ በዋሽንት፣ በከበሮ፣ በሪትምስቲክ ወዘተ… ዘፈኑን እንዲያጅቡ ማድረግ፣<br>• ተራ በማለዋወጥና ባህላዊ ሙዚቃውን በመቀያየር |

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| | | በመደጋገም እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• በመጀመሪያ በማፍጠን እንዲያጨበጭቡ፣ ቀጥሎም በዝግታ እንዲያጨበጭቡ፣ በማስከተል እንደገና በፍጥነት እንዲያጨበጭቡ እርምጃውንም እንደዚሁ ትዕዛዙን በማለዋወጥ ማሠራት፣<br>• በቡድን በቆሙበት ሁኔታ አንደኛው በቡድን በቦታ ላይ ሰራመድ ወዘተ... ሌላው የሩጫውን ሪትም ተከትለው እንዲያጨበጭቡ ማድረግ፣ የተማሪዎች ተራ በማለዋወጥና በመደጋገም ማሠራት፣ |
| • የባቄላ ከረጢት ወርውረው መቅለብን ሠርተው ያሳያሉ፣ | 4.2.2 የባቄላ ከረጢት ወርውሮ መቅለብ | • ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ማጨብጨብን የበለጠ በቡድን በመክፈል ለማለማመድ የአንድ ቡድን አባላት፣ ሲራመዱ የሌላው አባላት እንዲያጨበጭቡ በማድረግና ተራ በማለዋወጥ ማለማመድ፣ |
| • በቦታ ላይ በመሆንና በቦታ ላይ ገመድ መዝለልን አጨዋወትን ያሳያሉ፣ | 4.2.3 በቦታ ላይ ገመድ ዝላይ | • በራሳቸው የአወራወር ዘዴ የባቄላ ከረጢት ወርውረው እንዲቀልቡ ዕድል መስጠት፣ ትክክለኛውን የአወራወር ዘዴ በማሳየት ማለማመድ፣ |
| • ትክክለኛ የእርሳስ አያያዝና አጠቃቀምን ያሳያሉ፣ | | • በቦታ ላይ ዝላይንና ገመድ ዝላይን በራሳቸው ዘዴ እንዲሠሩ ማድረግ፣ ትክክለኛውን የአዘላለል ዘዴ በማሳየት በነጠላ፣ በጥንድ በቡድን ሆነው ገመድ እንዲዘሉ ማድረግ፣ |
| • በመሞነጫጨር ለሚፈጥሩት ምስል የራሳቸውን ትርጉም በመስጠት ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፣ | 4.2.4 በእጅ መሞነጫጨር | • በውድድር መልክ የተሻለ የአዘላለል ዘዴ የሚጠቀሙትን ተማሪዎች ለሌሎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣ |
| • ሚዛን ጠብቆ በሁለት እግር ዘሎ በሁለት እግር ማረፍን ሠርተው ያሳያሉ፣ | 4.2.5 ሚዛን መጠበቅ<br>• በሁለት እግር ዘሎ በሁለት እግር ማረፍ | • ሚዛን በመጠበቅ በሁለት እግር ዘሎ በሁለት እግር ማረፍን እንዲሰሩ ማድረግ፣<br>• ትክክለኛውን የአዘላለል ዘዴ በሥዕል ወይም ሠርቶ በማሳየት እንዲለማመዱትና እንዲያዳብሩት ማድረግ፣ |
| • ለዒላማ አነጣጥረው ይወረውራሉ፣ | 4.2.6 ኳስ ለዒላማ መወርወር፣ | • ኳስ ለዒላማ መወርወርን ሠርተው እንዲያሳዩ ማድረግ፣ ትክክለኛው የአወራወር ዘዴን ሰርቶ በማሳየት ማለማመድ።<br>• ኳስን በወንበር ላይ በተወሰነ ርቀት በማስቀመጥ ከተወሰነ ርቀት ላይ በመሆን ተማሪዎች በትንንሽ ኳሶች ወንበር ላይ የተቀመጠችውን ኳስ እንዲመቱና ከወንበር ላይ እንዲጥሉ በማድረግ ማጫወት፣ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • በሙዚቃ ምት ጡብ ጡብ ይሠራሉ፣ | **4.3. ሪትሚካዊ እንቅስቃሴዎች**<br>4.3.1 በሙዚቃ ምት ጡብ ጡብ | • በሙዚቃ ምት ጡብ ጡብ እንዲሉ ማድረግ፣ ሁሉም በየተራ እየወጡ እንዲሠሩት በማድረግ ማለማመድ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች

- ሥዕሎች፣ የባቄላ ከረጢት፣ ገመድ፣ እርሳስ፣ወረቀት፣ ኳስ

## ክትትልና ግምገማ፡-

- በእጅ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- እጅና እግርን ከማቀናጀት ጋር የተያያዙ ተግባራት መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በቦታ ላይ በመሆን መዝለላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የባቄላ ከረጢት ወርውረው መቅለባቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ለዒላማ መወርወራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የሰውነት እንቅስቃሴን ከሪትም ጋር አቀናጅተው መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

# የሥነ-ጥበብና ሰውነት ማጐልመሻ
# ትምህርት ሲለበስ

# 2ኛ ክፍል

## ምዕራፍ አንድ በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች *(60 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ተረድተው ስለተረዱት ነገር ይገልፃሉ፣
- በአካባቢያቸው ስላሉ ነገሮች እንቅስቃሴ፣ ድምፅ፣ ቀለምና ቅርፅ ይገልፃሉ፣
- የተለያዩ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ተረድተው በመዝሙር በንድፍና በእንቅስቃሴ ክህሎት ይሳተፋሉ፣

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ:-*<br>• በጐረቤት የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከ1-2 ይዘረዝራሉ፣<br>• በጐረቤታቸው የሚገኙ የሕፃናት፣ የወጣቶችና የአረጋውያን አካሄድና ድምፅ አስመስለው ይሠራሉ፣<br>• ሕፃናትን ወጣቶችና አረጋውያንን ከመንከባከብ ጋር የተያያዙ ከ1-2 መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣ | **1.1 በጐረቤት አካባቢ የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች**<br>*(23 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.1.1 ሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን | • ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እንዲዘረዝሩ ዕድል መስጠት፣<br>• በሰፈር/አካባቢ የሚገኙ ስለ ሕፃናት፣ ወጣቶች/ልጆች/ አረጋውያን አነጋገር፣ አካሄድ፣ ድምፅ አለባበስ ወዘተ.. እንዲገልጹና በተግባርም የሚያውቁትን እንዲያሳዩ ማበረታታት፣<br>• የተማሪዎችን ሐሳብ መነሻ በማድረግና በማድነቅ በአካባቢያቸው/ጐረቤት የሚገኙ ሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን ተማሪዎችን ሊስብ በሚችል ኤስቴቲካዊ በሆነ መንገድ የሕፃናትን፣ ወጣቶችንና አረጋውያንን ዋና ዋና ተግባራት ገለፃ ማድረግ፣<br>• ለሕፃናትና ወጣቶች እንዲዚሁም ለአረጋውያን በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚደረገውን ከበሬታና እንክብካቤ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግና በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ |
| • መዝሙሩ የሚያስተላልፋቸውን መልዕክቶች ከ2-3 ይዘረዝራሉ፣<br>• ለሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን መደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ይዘምራሉ፣ | 1.1.2 መዝሙር/ስለሕፃናት፣ ልጆችና አረጋውያንን/ | • ከመልካም ሥነ ምግባር በተለይም ከሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን መልካም ሥራና እንክብካቤ ጋር የተያያዙ ቀላል መዝሙሮች እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• ከሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን መልካም ሥነ ምግባር ጋር የተያያዙ ገፀ ባሕርያትን በማዘጋጀት ድራማ ተለማምደው እንዲሠሩ ማበረታታትና የሠሩትንም በክፍሉ ተማሪዎች ፊት እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ |
| • ከ1-2 የሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን ድምፅ፣ እንቅስቃሴና ተግባራትን በድራማ ሠርተው ያሳያሉ፣ | 1.1.3 ድምፅና እንቀስቃሴን አስመስሎ መሥራት | • ስለ ሕፃናት ወጣቶችና አረጋውያን የተመለከቱትን በራሳቸው መንገድ ምስሎችን በንድፍና በቀለም ቅብ እንዲሠሩና የሠሩትንም ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያስረዱ ማድረግ፣ |
| • የሕፃናት ወጣቶችና አረጋውያንን ምስል በንድፍ ሠርተው ያሳያሉ፣ | 1.1.4 ንድፍ | |
| • በአካባቢያቸው የሚገኙ የዱር እንስሳትን | **1.2 በአካባቢያችን የሚገኙ የዱር እንስሳት** | • ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቁትን የዱር እንስሳት |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| ከ2-3 ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ የዱር እንስሳትን ስም ከ2-3 ድምፅና እንቅስቃሴ አስመስሎ በመሥራት ያሳያሉ፣<br>• ስለዱር እንስሳት የሚገልፅ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት በመዘመር ያሳያሉ፣<br>• ከ2-3 የዱር እንስሳትን ምስል በራሳቸው መንገድ በንድፍ ሠርተው ያሳያሉ፣ | *(17 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.2.1 ድምፅንና እንቅስቃሴን አስመስሎ መሥራት<br>1.2.2 የዱር እንስሳት መዝሙር<br>1.2.3 በንድፍ አስመስሎ መሥራት | ዓይነት፣ ቀለማትና አኗኗር እንዲዘረዝሩ ጥያቄ ማቅረብ፣<br>• የመረጡትን የዱር እንስሳ ድምፅን በማስመሰል እንዲያሰሙ ማድረግ፣ ከዚያም የዱር እንስሳቱን እንቅስቃሴ፣ አረማመድና አሯሯጥን እንዲገልጹና አስመስለው እንቅሰቃሴውን እንዲያሳዩ ማበረታታት፣<br>• ከዱር እንስሳት ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን እንደ መዝሙሮቹ ቅለትና ክብደት ተገቢ የሆኑ መዝሙር የማስተማር ዘዴዎችን በመምረጥ ማለማመድ፣ መዝሙሩን ከተለማመዱ በኋላ ከቀላል የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችና እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• የፈለጉትን የዱር እንስሳት ምስልን በራሳቸው ዘዴ አስመስለው እንዲሠሩና የሠሩትንም የዱር እንስሳ ምስል ስለ አሰራሩ በቅደም ተከተል ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያስረዱ ማድረግ፣ |
| • በአካባቢያቸው ለኤስቴቲክስ መሣሪያዎች መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ይዘረዝራሉ፤<br>• ከ2-3 በአካባቢያቸው የሚገኙትን ቁሳቁሶችን በመጠቀም<br>- ኳስችንና ገመዶችን<br>- የማጨብጨቢያ ጣውላና ፀናጽል<br>- ቅርፃቅርጽ፣ ቀለማትና ብሩሽን ያዘጋጃሉ፣<br>• የእያንዳንዱን መሣሪያ አሠራር ሂደት ይገልጻሉ፣<br>• ባዘጋጁት መሣሪያዎች ተጠቅመው የተለያዩ ኤስቴቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ፣ | **1.3 ከአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን መጠቀም***(20 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.3.1 ለአስቴቲክስ መሣሪያዎች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት<br>• የመዝለያ ገመዶችን<br>• ኳሶች<br>• የተለያዩ ቀለማት<br>• የማጨብጨቢያ ጣውላ<br>• ፀናጽል<br>• ቅርፃቅርጾች<br>• ቀለማት<br>• ብሩሽ | • ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድና ተሞክሮ ተነስተው በአካባቢያቸው የኤስቴቲክስ መሣሪያዎችን ለመሥራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• ተማሪዎች የኤስቴቲክስ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት በአካባቢያቸው የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችና ቁሳቁሶች ዝርዝር ላይ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ በቡድናቸው የደረሱበትን ፍሬ ሐሳቦች ለክፍላቸው ተማሪዎች በቅደም ተከተል እንዲገልጹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መርዳት፣<br>• የኤስቴቲክስ ሞዴል መሣሪያዎችን ሥዕሎችን ወዘተ... ማሳየት፣ ባዩት መሠረት በቡድን ተከፋፍለውና ለመሥሪያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በቅድሚያ አሟልተው የተመረጡትን የሚስተማሪያ መሣሪያዎች እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን ተጠቅመው የኤስቴቲክስ መሣሪያዎችን ሠርተው እንዲያመጡ ሥራ በመስጠት መከታተል፣ ሠርተው ስላመጡት መሣሪያዎች ስለአሠራሩ ለክፍሉ ተማሪዎች ገለፃ እንዲሰጡ ማድረግና ተማሪዎች ሠርተው ባመጡት ላይ የክፍላቸው ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት |

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| | | ማድረግ። በጥሩ ሁኔታ ሠርተው ያመጡ ተማሪዎችን እንደሞዴል በመውሰድ ሌሎችም የእነሱን አርአያ ተከትለው እንዲሠሩ ማበረታታት፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ምስሎች
- ቻርቶች
- ሞዴሎች
- በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶችና ጥሬ ዕቃዎች
- የተለያዩ ቀላል የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች

## ክትትልና ግምገማ፡-

- በጐረቤት/አካባቢ የሚገኙ ሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን አካሄድ፣ አለባበስና የሥራ ድርሻ መዘርዝራቸውን በቀላ ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- የአረጋውያን፣ ልጆችና ወጣቶችን የሚያወሳ መዝሙር መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ስለ ልጆች፣ ወጣቶችና አረጋውያን መልካም ሥነ ምግባርና ሥራ በድራማ ሠርተው ማሳየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ሕፃናት ወጣቶችና ሐረጋውያን ምስል በንድፍ መሥራታቸውን የሥራ ውጤታቸውን በማየት ማረጋገጥ፣
- በአካባቢያቸው የሚገኙ የዱር እንስሳትን ምስል፣ ድምፅና እንቅስቃሴን አስመስለው መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ስለዱር እንስሳት የሚያወሳ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው መዘመራቸው በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የኤስቴቲክስ መሣሪያዎችን ማዘጋጀታቸውንና መጠቀማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ።

## **ምዕራፍ ሁለት፡- ባህልና ቅርስ** *(40 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የምጠበቁ ወጤቶች፡-*** *ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- *የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን ተገንዝበው ይጫወታሉ፣*
- *በባህላዊ ጨዋታዎችና ጭፈራዎች የመሣተፍ ልምድና ክህሎትን በማዳበር በጫወታው ይሳተፋሉ፣*
- *ባህላዊ ስፖርቶችና እንቅስቃሴዎችን የሚያዘውትሩና በመዝናናት የመጠቀም አዎንታዊ ዝንባሌን በተግባር ያሳያሉ፣*

| ***የሚጠበቅ አጥጋቢ የቸሎታ ደረጃ*** | ***ይዘቶች*** | ***የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች*** |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• ከ1-2 በአካባቢያቸው/ጐረቤታቸው የሚዘወተሩ የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን አይነት ይዘረዝራሉ፣<br>• የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፣<br>• 2-3 በአካባቢያቸው የተለመዱ ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን ይጫወታሉ፣ | **2.1 የባህላዊ ጨዋታዎች ዓይነትና የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች**<br>*(40 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.1.1የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች<br>2.1.2 በንድፍ አሰመስሎ መሥራት | • በተለያዩ ወቅቶች የሚዘወተሩ ባህላዊ የልጆች ጨዋታዎች እነማን እንደሆኑ መቼ እንዲሚጫወቷቸው እንዴት እንደሚጫወቱ መጠየቅ፣<br>• ሌሎች ያልተጠቀሱ ካሉም ወላጆቻቸውን ወይም ሌላ ሰው ጠይቀውና ጽፈው እንዲመጡና ለክፍሉ እንዲያስረዱ እድል መስጠት፣<br>• ለጨዋታው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች በማሟላት በየቡድን ሆነው እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ |
| • ለባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች ያላቸው አድናቆት በራሳቸው መንገድ በሥዕል ይገልጻሉ፣<br>• ከ1-2 የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን በራሳቸው መንገድ በንድፍ ምስሎችን ሠርተው ያሳያሉ፣ | **2.2 ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች**<br>2.2.1 በንድፍ አስመስሎ መሥራት | • የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን የሚገልፁ ንድፎችን ርዕስ በመስጠት ሠርተው እንዲያቀርቡ የፕሮጀክት ሥራ መስጠትና ሥራቸውን አወዳድሮ የተሻሉትን በሌሎች ማስጐብኘት፣<br>• በአካባቢያቸው የሚዘወተሩ ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች እንዲዘረዝሩና መቼ እንደሚጨፈሩ መጠየቅ፣ |
| • ከ1-2 በአካባቢው የሚዘወተሩ ባህላዊ ስፖርታዊ ጨዋታ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢው የሚታወቁ ባህላዊ ስፖርቶችን በመጫወት ያሣያሉ፣<br>• ከ2-3 የባህላዊ ስፖርቶቹን አጨዋወት መሠረታዊ ህጐች ይዘረዝራሉ፣<br>• ጨዋታዎቹን በራሳቸው መንገድ በንድፍ የሰራሉ፣ | 2.3 ባህላዊ ስፖርታዊ ጨዋታዎች<br>2.3.1 በንድፍ አስመስሎ መሥራት | • ለሠርግ ለተለያዩ በዓላት የሚዘወተሩ የተቀረፁ ባህላዊ ዘፈኖችን መከፈትና ተማሪዎች በቡድን እንዲጫወቱ ማድረግ<br>• ተማሪዎችን በቡድን መመደብና እያንዳንዱ ቡድን የራሱን ባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ተለማምዶ በማቅረብ እንዲወዳደሩ ሁኔታዎች ማመቻቸት፣<br>• በተግባራዊ እንቀስቃሴ ያሳዩትን በራሳቸው መንገድ በንድፍ እንዲገልጹት የክፍልና የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• ተማሪዎች ባህላዊ የስፖርት ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ ጥያቄዎችን በማቅረብ ማበረታታት፣ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • ጨዋታዎችን ለመጫወት ተነሳሽነታቸውን በማሳየት ይጫወታሉ፣ | | • የዘረዘሩዋቸውን ባህላዊ የስፖርት ጨዋታዎችን ተጫውተው እንዲያሳዩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተገቢውን እገዛ ማድረግ፣<br>• ለባህላዊ የስፖርት ጨዋታዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በማሳወቅ በጨዋታ ወቅት እንዲጠቀሙባቸው ማድረግና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ለባህላዊ ዘፈኖች የሚያገለግሉ መሣሪያዎች /ቴፕሪኮርደር በካሴት የተቀረጹ ባህላዊ ዘፈኖች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች/
- ባህላዊ ስፖርት ቁሳቁሶች
- ሞዴሎች ቻርቶችና ፎቶግራፎች ወዘተ...

## ክትትልና ግምገማ፡-

- የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን መዘርዘራቸውን ለማወቅ በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ ጨዋታዎችና ባህላዊ ስፖርቶችን መዘርዘራቸውን በጥያቄና መልስ ማረጋገጥ፣
- የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በህላዊ ዘፈኖችንና ጭፈራዎችን ደስተኛ ሆነው መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- እንቀስቃሴዎቹን በራሳቸው መንገድ በንድፍ መግለጽ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የክፍል/የቤት ሥራ በመስጠት በማረም መስራታቸውን መረጋገጥ፣

## ምዕራፍ ሦስት፡- ጥንቃቄና ደህንነት *(22 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ወጤቶች፡-*** *ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- *አካባቢያቸውን በንጽህና የመጠበቅ ፍላጐትና ዝንባሌ በማሳያት ተግባራዊ ያደርጋሉ፣*
- *አካባቢን በንጽህና ስለመጠበቅ አስፈላጊነት ያላቸውን ስሜትና ሐሣብ በንድፍ ሠርተው ያሳያሉ፣*
- *ዜማን ጠብቀውና ግጥሞችን አስታወስው በህብረት ይዘምራሉ፣*
- *በጤናና በአካል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ተገንዝበው ስለተፈላጊው ጥንቃቄ ስሜታቸውን በንድፍና በእንቅቃሴ ይገልፃሉ፣*
- *የኤች አይቪ ኤድስ ተጠቂ የኀብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፣*

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• *የአካባቢን ንጽሕና ጠቀሜታ* ከ2-3 *ይዘረዝራሉ፣*<br>• *ስለ አካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ የሚያወሳ መዝሙር በእንቅስቃሴ በማጀብ ይዘምራሉ፣*<br>• *መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ይገልጻሉ፣* | **3.1 የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ**<br>*(9 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.1.1 *መዝሙር*/4 ክፍለ ጊዜ/ | • *ስለ ጥንቃቄና ደህንነት ተማሪዎች ከሚያውቁት ነገሮች በመነሳት ገለፃ ማድረግ፣*<br>• *ተማሪዎች ስለአካባቢ ንጽሕና የሚያውቁትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ ለምሳሌ የአካባቢያቸውን ንጽህና ይጠብቁ እንደሆነ በምን ዓይነት መንገድ እንደሆነ ወዘተ.. መጠየቅ፣*<br>• *ከተማሪዎች ልምድና ተሞክሮ በመነሳት ከአሁን በፊት ስለአካባቢ ንጽሕና የሚያውቁት መዝሙር ካለ በማስታወስ እንዲዘምሩ እድል መስጠት፣*<br>• *ስለ አካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ የተዘጋጀውን መዝሙር ለማዘመር ተስማሚ የሆነውን የማስተማር ዘዴ በመምረጥ ተማሪዎቹን በቡድን ከፋፍሎ ማለማመድ፣* |
| • *ከአካባቢ ንጽሕና ጋር የተያያዙ ምስሎችን በንድፍ አስመስለው ሠርተው ያሳያሉ፣*<br>• *የአካባቢን ንጽሕና የሚገልጽ ድራማ ሠርተው ያሳያሉ፣* | 3.1.2 *በንድፍ አስመስሎ መሥራት*/3 ክፍለ ጊዜ/<br><br>3.1.3 *ድራማ*/2 ክፍለ ጊዜ/ | • *ከአካባቢ ንጽሕና ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን በራሳቸው መንገድ/በምስል/ ንድፍ አስመስለው እንዲሠሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተገቢውን እገዛ ማድረግ፣*<br>• *የአካባቢን ንጽሕና አጠባበቅ የሚገልጽ ድራማ ገፀ ባህርይ በማዘጋጀትና ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ማለማመድ በቡድን የተለማመዱትን ድራማ በክፍላቸው ተማሪዎቸ ፊት እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣* |
| • *የመንገድ ላይ ጥንቃቄዎችን* ከ2-3 *ይዘረዝራሉ፣*<br>• *ከመንገድ ደህንነት ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣*<br>• *ከመንገድ ጥንቃቄ ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን በራሳቸው መንገድ በንድፍ አስመስለው ይሠራሉ፣* | **3.2 በመንገድ ላይ አደጋ ከሚደርሱ ነገሮች መጠንቀቅ** *(6 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.2 .1 *መዝሙር*<br><br>3.2.2 *በንድፍ አስመስሎ መሥራት* | • *ተማሪዎች ስለመንገድ ጥንቃቄና ደህንነት ከራሳቸው ልምድ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግና በመንገድ ላይ መውሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣*<br>• *የተማሪዎችን ሐሳብ መነሻ በማድረግ በመንገድ ላይ መውሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ገለፃ ማድረግ፣*<br>• *ተማሪዎቹ ካሁን በፊት ስለመንገድ ደንነት ጥንቃቄ የሚያወሳ መዝሙር ያውቁ እንደሆን እንዲዘምሩ ማድረግ፣ ስለመንገድ ደህንነት የተዘጋጀውን መዝሙር ተስማሚ የሆነውን መዝሙር የማስተማር ዘዴን በመጠቀም* |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• ከመንገድ ጥንቃቄ ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን በራሳቸው መንገድ በንድፍ አስመስለው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣<br>• የሠሩትን ሥራ ለክፍላቸው ተማሪዎች እንዲያሳዩና እንዲያስረዱ ማድረግና የክፍሉ ተማሪዎችም አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ማድረግ፣ |
| • ዋና ዋና የኤች አይቪ ኤድስ ተጠቂ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ከ1-2 ይዘረዝራሉ፣ | **3.3 ኤች አይቪ/ኤድስ /7 ክፍለ ጊዜ/**<br>3.3.1 የኤች አይቪ/ኤድስ ተጠቂ የሕብረተሰብ ክፍሎች | • የኤች አይቪ/ኤድስ ተጠቂ የሕብረተሰብ ክፍሎች እነማን እንደሆኑ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>• በቡድን ውይይታቸው ላይ የደረሱበትን የኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን በቡድን መሪያቸው አማካይነት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣<br>• ተማሪዎች ካሁን በፊት ስለኤች አይቪ/ኤድስ የተዘመሩ መዝሙር ያውቁ እንደሆነ እንዲዘምሩ እድል መስጠት፣ |
| • ከኤች አይቪ/ኤድስ አስከፊነት ጋር የተያያዘ መዝሙር ይዘምራሉ፣<br>• የኤች አይቪ/ኤድስ ተጠቂ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤ በራሳቸው መንገድ በንድፍ አስመስለው ይሠራሉ፣ | 3.3.2 መዝሙር<br><br>3.3.3 በንድፍ አስመሥሎ መሥራት፣ | • ስለኤች አይቪ/ኤድስ የተዘጋጀውን መዝሙር እንደመዝሙሩ ቅለትና ክብደት አስፈላጊውን መዝሙር የማስተማር ዘዴን በመጠቀም ማለማመድ፣<br>• የኤች አይቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን በንድፍ አስመስለው እንዲሠሩ ተገቢውን እገዛ ማድረግ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ምስሎች፣ ቴፕሪከርደር፣ መዝሙር የተቀረጸባቸው ካሴቶች ወዘተ..

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ስለአካባቢ ንጽሕና ጠቀሜታ መዘርዘራቸውን በጥያቄና መልስ ማረጋገጥ፣
- ከአካባቢ ንጽሕና ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ከአካባቢ ንጽሕና ጋር የተያያዙ ድራማ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የአካባቢ ንጽሕና ምስሎችን መሥራታቸውን የሠሩትን ሥራዎች በማየት መገምገም፣
- በመንገድ ላይ አደጋ ከሚያደርሱ ነገሮች መጠንቀቅ የተያያዙ መዝሙሮች መዘመራቸውንና በራሳቸው መንገድ ንድፍ መሥራቻቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የኤች አይቪ/ኤድስ ተጠቂ የሕብረተሰብ ክፍሎች መዘርዘራቸውን፣ መዝሙር መዘመራቸውንና ምስሎችን በንድፍ መሥራታቸውን ማረጋገጥ፣

## ምዕራፍ አራት፡- የሰውነት ክፍሎች ተግባራት *(82 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የምጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በእጅ የሚከናወኑ ተግባራትን ተገንዝበው፣ እጅና እግርን በማቀናጀት በተግባር ሠርተው ያሳያሉ፣
- መሠረታዊ የምትና ነፃ እንቅስቃሴን አውቀው ይተገብራሉ፣
- ከሰውነት ክፍሎች ጋር የተያያዙ መሠረታዊ የኤስቴቲክስና እንቅስቃሴ ክህሎትን የሚያደብሩ ክንዋኔዎችን ሠርተው ያሳያሉ፣

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• ዋና ዋናዎቹን የሰውነት ክፍሎች ተግባራት ከ1-2 ይዘረዝራሉ።<br>• ቀላል የንድፍ፣ የቀለም ቅብና ሕትመት አሠራርን ከ1-2 ይዘረዝራሉ።<br>• የተመረጡትን ነገሮች በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ።<br>• ቀላል ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሕትመቶችን ሠርተው ያሳያሉ። | **4.1 በእጅ የሚከናወኑ ተግባራት**<br>*(22 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.1.1 ንድፍ፣ ቀለም ቅብና፣ሕትመት | • በእጅ የሚከናወኑ ተግባራትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>• የፈለጉትን ወይም የተመረጡትን ነገሮች ንድፍ አስመስለው እንዲሠሩ ማድረግ። ይህንንም ለመተግበር በመጀመሪያ ስለንድፍና ቀለም ቅብ ተማሪዎች በሚረዱት መንገድ በተግባር ማሳየት፣<br>• የፈለጉትን ምስል ከሰውነት ክፍሎች በመምረጥ በራሳቸው መንገድ መጀመሪያ በንድፍ ቀጥሎም ቀለም በመቀባት እንዲገልጹ ማድረግ፣<br>• የሠሩትን ምስሎች አሠራር ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ማድረግ፣<br>• በተሠራው ምስል ላይ ተማሪዎቹ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>• ስለሕትመት በተግባር ማሳየት ሕትመትን በተለያየ መንገድ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>ምሳሌ፡- የጣቶቻቸውን ጫፍ ቀለም እያስነኩ በወረቀት ላይ እንዲያትሙ ማድረግ። በባዶ ወረቀት ላይ ላጲስ፣ ሣንቲም፣ ወይም ቆርኪ በመጠቀም በማራራቅ የተለያዩ ቦታዎች ላይ በብዛት ካተሙ በኋላ እያንዳንዳቸውን ሕትመቶች በቀጥታ መስመር እንዲያገናኙዋቸው ማድረግ፣ የሠሩትን ለጓደኞቻቸው በማሳየት አስተያየት እንዲሰጥባቸው ማድረግ፣ |
| • የእጅን ተግባር የሚያወሳ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ይዘምራሉ፣ | 4.1.2 *መዝሙር፡-* | • ከእጅ ተግባራት ጋር የተያያዘ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲዘምሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ከመዝሙሩ ጋር የሚሄዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች በመፍጠር አቀናጅተው እንዲዘምሩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ተግባራዊ ማድረግ፣ |

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| • እጅና እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራት ከ1-2 ይዘረዝራሉ፣<br>• የሩጫ ምትን ከተለያዩ ምቶች ጋር በማቀናጀት በእንቅስቃሴ ሠርተው ያሳያሉ፣ | **4.2 እጅና እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራት** *(48 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.2.1 የሩጫ ምት | • እጅና እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ። በእጅና እግር ቅንጅት የሚሠሩ ዋና ዋና ተግባራትን ማስረዳት፣<br>• ቀላል የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሩጫ ምትን ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዱ ማድረግ። ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የሩጫ ምት ክንዋኔ ከእጅ ጭብጨባ፣ በምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ከበሮ፣ ፀናጽል ወዘተ... እንዲለማመዱ ማድረግ። የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዱ ማድረግ፣ |
| • ከመወርወርና መቅለብ ጋር የተያያዙ ተግባራትን በማቀናጀት ይሠራሉ፣<br>• ከመወርወርና መቅለብ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• በጨዋታው አማካይነት ከሌሎች ጋር በመተባበር መሥራትን በተግባር ሠርተው ያሳያሉ፣ | 4.2.2 የጨርቅ ኳስ ወርውሮ መቅለብ | • ስለ መወርወርና መቅለብ አሠራር የሚውቁትን እንዲያስረዱ፣ ማድረግ፣<br>• ከመወርወርና መቅለብ ጋር የተያያዙ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሠሩ ማድረግ፣ ምሳሌ፡- ኳስ ወይም ተመሳሳይ ነገር ከራስ በላይ እየወረወሩ እንዲቀልቡ ማድረግ፣<br>• በጥንድ ሦስት ለሦስት ወዘተ... በመሆን በመካከላቸው ያለውን ርቀት በመቀነስ ወይም በመጨመር እየወረወሩ እንዲቀባበሉ ማድረግ፣<br>• የአወራወር ዓይነቶችን በመቀያየር ማለትም በአንድ እጅ፣ በሁለት እጅ፣ ከታች ወደ ላይ፣ ከላይ ወደታች ወዘተ.. በየተራ ደጋግመው እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• የአወራወር አይነቶቹን አሠራር በገለፃና/በሠርቶ ማሳየት አስደግፎ እንዲረዱት ማድረግ፣<br>• መወርወርና መቅለብን በተመለከተ ኳስ በፈለጉበት መልክ ወደ ላይ እንዲወረውሩና ስትመለስ እንዲቀልቡት በማድረግ ማለማመድ፣<br>• ከተወሰነ ሙከራ ልምምድ በኋላ ሌላ ክንዋኔ ማስከተል ለምሳሌ ኳስ በሁለት እጅ ወርውሮ መቅለብ በአንድ እጅ ወርውሮ መቅለብን እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ቀስ በቀስ በተከታታይ የሚወረውሩትን ቁጥሩን በመጨመርና በመሀከላቸው ውድድር በመፍጠር እንዲለማመዱ ማድረግ፣ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • የገመድ የመዝላይ እቅንቅስቃሴን ለ30 ሰከንድ ሠርተው ያሳያሉ፣<br><br>• የገመድ ዝላይ ከመዝሙርና ከዝላይ ምት ጋር አቀናጅተው ይሠራሉ፣<br><br>• ከመወርወርና መቅለብ እና ከዝላይ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ የክንዋኔ ትይንቶችን በራሳቸው መንገድ መስመሮችን በመጠቀም የተለያዩ ምስሎችን ይሠራሉ፣<br>• የሠሩትን ምስሎች አሠራር<br>• ይገልጻሉ፣<br>• በአንድ እግር ቆሞ እጆችን ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ይዘረጋሉ፣ | 4.2.3 የገመድ ዝላይ<br><br>4.2.4 ንድፍ/በመስመር ዓይነቶች የተለያዩ ምሥሎችን መሥራት/ | • ተማሪዎች ካሁን በፊት የገመድ ዝላይ እንቅስቃሴን ያውቁ እንደሆነ ሰመጠየቅ የራሳቸውን ልምምድ እንዲገልጹና በተግባርም እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ለዝላይ ተስማሚ የሆነውን የሙዚቃ ምት የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ጭብጨባ፣ ከበሮ በመጠቀም ተማሪዎች ከገመድ ዝላይ እንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• በመጀመሪያ መዝሙሩን ከገመድ ዝላይ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲዘሉ ማድረግ፣<br>• የመወርወርና መቅለብ እና ዝላይ እንቅስቃሴዎችን ምስሎች በራሳቸው መንገድ ሠርተው እንዲያሳዩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሠሩ በማድረግ አሠራሩን ማሳየት፣<br>• የሠሩትን ሥራዎች በማየት አስፈላጊውን እርምት ማድረግ፣ |
| | 4.2.5 ሚዛን መጠበቅ<br>• በአንድ እግር ቆሞ እጆችን ወደተለያዩ አቅጣጫዎች መዘርጋት፣ | • በአንድ እግር በመቆምና እጆችን ቀጥ አድርጐ ወደ ጐን ወደ ላይ ወደፊት በመዘርጋት የሚከናወኑ ሚዛን የመጠበቅ ተግባራትን ማሳየት፣<br>• ተማሪዎች ትክክለኛውን አሠራር ተክተለው ሚዛን የመጠበቅ ልምምድ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • ወደ ተለያየ አቅጣጫ በትክክል የሰውነት ከፍሎቻቸውን ያሽከረክራሉ፣ የአሠራሩንም ቅደም ተከተል ይገልፃሉ፣<br>• ኳሶችን በእግር ለጓደኞቻቸው ያቀበላሉ፣<br>• የተመታላቸውን ኳስ በማቆም መልሰው ያቀብላሉ፣ | 4.2.6 ኳስ መቀባበል | • ተማሪዎች ሁለት ሆነው በመቀጥ በርቀት ትይዩ ሆነው እንዲቆሙ በማድረግ አንዱ ኳስ መትቶ ለጓደኛው ሲያቀብል ሌላው ጓደኛው ኳስ በማቆም መልሶ እንዲያቀብል በማድረግ ማሠራት<br>• በተማሪዎች መካከል ያለውን ርቀት በመጨመር ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• እንቅስቃሴውን በንድፍ እንዲገልፁ ማድረግ፣ |
| • ከግልቢያ ምት ጋር የተያያዙ | **4.3 ሪትማካዊ እንቅስቃሴዎች** | • የግልቢያ ምት በማፍጠንና ዝግ በማድረግ ተማሪዎቹ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| እንቅስቃሴዎችን ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• ሙዚቃን በማድመጥ ነፃ እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ፣<br>• እንቅስቃሴዎቹን በራሳቸው መንገድ በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ፣ | *(12 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.3.1 የግልቢያ ምት<br><br>4.3.2 በሙዚቃ ነፃ እንቅስቃሴዎች | ለሚሰሙት ምት ተስማሚውን እንቅስቃሴ እንዲያሰሩ ማድረግ፣<br>• ልዩ ልዩ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ከበሮ፣ ሪትም እስቲክና ፀናጽል ወዘተ... በመጠቀምና ተማሪዎች ወደ ተለያየ አቅጣጫ በጥንድና በቡድን በመሆን ደጋግመው እንዲለማመዱ<br>• ማድረግ፣<br>• በሙዚቃ የተቀነባበሩ ዘፈኖችን በማስደመጥ ነፃ እንቅስቃሴዎችን እንዲሠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ኳሶች፣ ቆርኪዎች፣ ቁልፎች፣ ሥዕሎች፣ ቻርቶችና የመዝለያ ገመድ
- የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ፣ ቴፕርኮደር፣ መዝሙር የተቀረጸባቸው ካሴቶች ወዘተ...

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ዋና ዋናዎቹን የሰውነት ክፍሎች ተግባራት መዘርዘራቸውን በጥያቄና መልስ ማረጋገጥ፣
- ከሰውነት ክፍሎች የተመረጡትን በንድፍና በቀለም ቅብ መሥራታቸውን ለማረጋገጥ የቤት ሥራ መስጠትና መሥራታቸውን በማረም ማረጋገጥ፣
- ቀላል ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሕትመቶችን ሠርተው ማሳየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የእጅን ተግባር የሚገልጽ መዝሙር መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ከመቅለብና ከመወርወር ጋር የተያያዙ እንቅቃሴዎችን መዝሙር መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- መሥመሮችን በመጠቀም የተለያዩ ምስሎችን መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ሚዛን መጠበቅና ኳስ መቀባበልን መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በሙዚቃ ምት የግልቢያ እንቅስቃሴ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

# የሥነ-ጥበብና ሰውነት ማጎልመሻ
# ትምህርት ሲለበስ

# 3ኛ ክፍል

## *ምዕራፍ አንድ፡-በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች (41 ክፍለ ጊዜ)*

*ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- የተለያዩ ሙያዎች ለሀገርና ለኀዝብ እንደሚጠቅሙ ተገንዝበው ተፈላጊውን ክብር ይሰጣሉ፣
- ዮሙያተኞችን ተግባራት ተረድተው አስመስለው ይሠራሉ፣ ስለተግባራቸውም ይዘምራሉ፣
- በአካባቢ የሚገኙ ዕፅዋትን ቀለምና ቅርፅ ያላቸውን ውጤት ተገንዝበው አስፈላጊውን የጥንቃቄ ዘዴዎቹን ይገልጻሉ፣
- ቀላል የመገልገያ ቁሣቁሶችን በራሣቸው ለማዘጋጀትና አካባቢን የመጠቀም ልምድን በተግባር ሠርተው ያሳያሉ፣
- በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ነገሮች ያላቸውን ግንዛቤ በራሣቸው የችሎታ መጠን በንድፍ ለመግለጽ እንዲችሉ መሠረታዊ የአሠራር ቅደም ተከተሉን ይገልጻሉ፣

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• በአካባቢያቸው ስላሉ ሙያተኞች ምንነትና አስፈላጊነት ከ2-3 ይገልፃሉ፡፡<br>• ስለሙያተኞቹ አስፈላጊነትና ዕኩልነት የሚገልፁ መዝሙሮችን ግጥምና ዜማ አስታውሰው ይዘምራሉ፡፡<br>• ከ2-3 የሙያተኞችን የሥራ ውጤት በንድፍ ይሠራሉ፣ | 1.1 **በቀበሌ የሚገኙ ሙያተኞች**<br>*(10 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.1.1 የሙያተኞች ተግባራት.<br>1.1.2 መዝሙር<br>1.1.3 ድራማ<br>1.1.4 ንድፍና ቀለም ቅብ | • ቤተሠብን ጨምሮ በአካባቢያቸው ያሉት ሰዎች በምን ዕለታዊ ሥራ ላይ እንደተሠማሩ እንዲዘረዝሩ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• ሠርተው ያመጡትን ለክፍሉ ተራ በተራ እንዲያቀርቡ በመጠየቅ በቀረቡት የሙያ ዓይነቶች አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታና ባህርይ ላይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ውይይት ማድረግ፣<br>• በሙያዎች አስፈላጊነትና እኩልነት ላይ የተመሠረቱ የተዘጋጁ መዝሙሮችን ማስጠናትና በኀብረት እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• እያንዳንዱ ተማሪ አንድ የሙያ ዓይነት መርጠው በውይይትና በመዝሙር ያገኙትን ግንዛቤ በንድፍ በመሣላቸው መልክ ሠርተው እንዲያቀርቡ ጊዜ መስጠት<br>• ሥራቸውን በቀለማት እንዲያስውቡና ለውድድር እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣ |
| • በአካባቢያቸው ያሉ ዕፅዋትን በጠቀሜታቸው በቀለማቸው እና በቅርጻቸው ይለያሉ፣<br>• ዕፅዋትን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባ ያስረዳሉ፣<br>• የዕፅዋትን ጠቀሜታና እንክብካቤ የተመለከቱ መዝሙሮችን ግጥሞችና ዜማቸውን በማስታወስ በኀብረት ይዘምራሉ፡፡<br>• ከ2-3 የሚሆኑ የዕፅዋቱን ቅጠሎች ቀለማት ንድፎችን በንድፍና ቀለም ቅብ ይሠራሉ፣ | 1.2 በአካባቢ የሚገኙ ዕፅዋት<br>*(11 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.2.1 ስለዕፅዋት ጠቀሜታና ውበት መዝሙር፣<br>1.2.2 የዕፅዋቶችን እንቀስቃሴ አስመስሎ መሥራት<br>1.2.3 ንድፍና ቀለም ቅብ | • ተማሪዎችን ከክፍል ውጪ ዕፅዋት በብዛት ወደሚገኙበት መስክ /ጫካ/ መውሰድና በአካባቢው የሚገኙትን ዕፅዋት እንዲያስተውሉ ማድረግ፣<br>• የዕፅዋቱን መጠን፣ የቅጠሎቻቸውን ቅርፅ፣ ቀለማቸውን ወዘተ. በተመለከተ ጥያቄዎችን በማንሣት እንዲለዩና እንዲያነፃፅሩ ጊዜ መስጠት፣<br>• ዕፅዋቱን እየተመለከቱ በወረቀት ላይ እንዲነድፉ ማድረግ፣<br>• ዕፅዋቱን አስመስለው የነደፉትን ሥዕል የተለያዩ ቀለማትን በመቀባት ቅጠሎችን እንዲያስውቡ እገዛ ማድረግ፣<br>• ወረቀት ላይ የዕፅዋት ምስል በመንደፍ እላዩ ላይ ቅጠሎችንና እንጨት በማጣበቅ በኮላዥ መልክ ስዕሎችን እንዲሠሩ ማድረግ፣ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • ከ3-4 የሚሆኑ የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ንድፍ ነድፈው ቀለም ቀብተው ያሳያሉ፣ | **1.3 በአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን በመጠቀም የኤስቴቲክስ መሣሪያዎች አዘገጃጀት**<br>• መረብ<br>• ብሩሾች<br>• ቀለማት<br>• ማራካሽ<br>• ክራር<br><br>1.3.1 ንድፍና ቀለም ቅብ | • ስለዕፅዋት አስፈላጊነት ውጤት ጠቀሜታ በተረዱት መሠረት ግጥሞችን አዘጋጅተው ዜማ ደርሰውና መዝሙር አዘጋጅተው እንዲመጡ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• አዘጋጅተው ያመጡትን ማወዳደርና የተሻለውን እንዲመ ርጡ በማድረግ ሁሉም እንዲለማመዱት ማመቻቸት፣<br>• ስለ ዕፅዋት የተዘጋጁ መዝሙሮችን ማስደመጥና ተለማምደው እንዲዘምሩ ዋና ዋና መልዕክቶችም ላይ እንዲወያዩ ማድረግ::<br><br>• ባዩትና በተረዱት መሠረት በአካባቢያቸው ከሚገኙ ጥቅም አይሰጡም ተብለው ከተጣሉ ቁሳቁሶች ብሩሾች፣ ማራካሽ፣ ቀለበቶች፣ የገበጣ መጫወቻ፣ የከበሮ ሞዴል፣ የክራር ሞዴል እና የተለያዩ ዲዛይኖች እንዲሠሩ የክፍል ሥራና የቤት ሥራ መስጠት፤ በዚህን ጊዜ ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ መንገር:: ይኸውም የታሸጉ የተቀበሩ ወይም የተከለከሉ ቦታዎች ውስጥ ያሉ ቁሳቁስን በፍጹም እንዳይነኩ ማሳሰቢያ መስጠት:: ከዚህም በተጨማሪ በሥራው ወቅት በስለታማ ነገሮች እንዳይቆረጡ አስፈለጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማስገንዘብ::<br><br>• እያንዳንዱን መሣሪያ ሲሠሩ የአሠራሩን ሂደት ቅደም ተከተል አንዲያስተውሉና ግንዛቤ አንዲጨብጡ ማድረግ፣<br>• በመጽሐፉ ውስጥ ባሉት ይዘቶች ተስማሚ በሆኑ የትምህርት ርዕሶች እነዚህን መሣሪያዎች እንዲጠቀሙ ማድረግ::<br>• የመረብ፣ ብሩሽ፣ ማራካሽና ክራር ንድፍ እንዲነድፉ ማድረግ ቀጥሎም የነደፉትን መሣሪያ ቀለም እነዲቀቡ ማድረግ፣ |

**የማስተማሪያ** *መሣሪያዎች:-*

- *ፖስተሮች /የተለያዩ ሙያተኞችን ሥራ የሚያመለክቱ/*
- *ለንድፍና ለቅብ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች*
- *ቴኘሪኮርደርና ካሴቶች*
- *የማስተማሪያ ቁሣቁስ ለመስራት የሚጠቅሙ በአካባቢ የሚገኙ ቁሣቁሶች*

**ክትትልና** *ግምገማ:-*

- *ሙያተኞች ለኀብረተሰቡ የሚሠጡትን ጠቀሜታ የሚገልፁ መዝሙሮችን ከእንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው መዘመር መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *ስለሙያዎች በመዝሙር የገለፁትን ሀሳብ በቃል እንዲገልፁ መጠየቅ*
- *አንድ ሙያ ከሌላው ሙያ ይበልጣል/አይበልጥም የሚለውን የመከራከሪያ ሃሣብ በማንሣት የማሣመኛ ነጥቦችን እያቀረቡ መራከራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *ስለ ሙያዎች አይነት ያላቸውን ስሜት ምን ያህል በንድፍ መግለጽ መቻላቸውን የቀለም አመራረጣቸውንና የንድፎቻቸውን ምጣኔ መሻሻል በምልከታ መከታተልና ማረጋገጥ፣*
- *ስለዕፅዋት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ ከመልሣቸው ማረጋገጥ*
- *የዕፅዋትን ምስል አስመስለው ሲሰሩ፣ ሲቀቡ፣ ሲለጥፉ ምን ያህል እንደሚያስተውሉና እጆቻቸውን የመጠቀም ችሎታቸው ምን ያህል እንደተሻሻለ በምልከታ ማረጋገጥ::*
- *በአካባቢያቸው በሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችና ቁሳቁሶች የማስተማሪያ መሣሪያዎችን መሥራታቸውንና ስለአሠራራቸው መግለጽ መቻላቸውን ለማረጋገጥ በቃል ወይም በጽሑፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣*

## ምዕራፍ ሁለት፡- ባህልና ቅርስ *(27 ክፍለ ጊዜ)*

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-* ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ:

- የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን በመረዳት በቡድን ይጫወታሉ፣
- በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎችንና አጨፋፈራቸውን ተገንዝበው ይጫወታሉ½
- ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ጠቀሜታን ማወቅ በአካባቢ በሚገኙ ጥሬ እቃዎች መሣሪያዎቹን ያዘጋጃሉ፣
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ ጨዋታዎች በጋራ በመጫወት ማኅበራዊ ግንኙነታቸውን ያንፀባርቃሉ፣
- የባህላዊ ቅርሶች ምንነትና ጠቀሜታ ተረድተው ይገልጻሉ፣

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• ከ1-2 የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ጨዋታዎችን በኅብረት የመጫወት ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• ከልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች ጋር የሚሄዱ እንቅስቃሴዎችና ጭፈራዎችን ከተለያዩ ሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በማቀናጀት ሠርተው ያሳያሉ::<br><br>• የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች በራሳቸው መንገድ ከአልባሳት እና ከመሣሪያዎች አጨዋወት ጋር የተያያዙ ምሥሎችን በራሳቸው መንገድ ይሠራሉ:: | 2.1 የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች<br>*(6 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.1.1 ንድፍና ቀለም ቅብ | • የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲለዩ የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች በመጠየቅ ማወያየት፣<br>• በዘመን መለወጫ: በመስቀል: በቡሄ ወዘተ.. በዓላት ላይ ምን ዓይነት ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ ? ምን ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያዎች እና አልባሳት ትጠቀማላችሁ?<br>• ከነዚህ ጨዋታዎች መካከል የተወሰኑ ተማሪዎች ወጥተው እየተጫወቱ እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ሴቶች ብቻ የሚጫወቱዋቸውን ባህላዊ የልጆች ጨዋታዎች ሴቶች ልጆች ወጥተው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማበረታታት፣ እንዲሁም ወንዶች ልጆች ብቻ የሚጫወቱዋቸውን ጨዋታዎች ወንዶች ልጆች ተጫውተው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ሌሎች ባህላዊ የልጆች ጨዋታዎች ግጥም ከሌሎች ሰዎች በመጠየቅና የሚያስፈልጉ አልባሳትና ቁሳቁሶች ይዘው እንዲመጡ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• ባህላዊ ጨዋታዎችን በቡድን ተለማምደው ለሌሎች እንዲያሳዩ ማድረግ:: ጭፈራዎችን በተገቢ መሣሪያዎችና አልባሳት እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣<br>• ተማሪዎቹ ባህላዊ አልባሳትን ለብሰው የሙዚቃ መሣሪያዎቹን በመጫወት ባህላዊ ጨዋታውን ሲጫወቱ የሚያሳዩ ምስሎች በንድፍና በቀለም ቅብ/ሠርተው እንዲያሳዩ ማድረግ:: ከሥራዎች መካከል የተሻለ የተሠራውን በጋራ መምረጥ:: |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • ከ1-2 የሚሆኑ ባህላዊ የሠርግ ጨዋታ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎችንና ዘፈኖችን ግጥምና ዜማዎችን ለይተው በኅብረት ከ1-2 ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፣<br>• ስለባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎች የተረዱትን በንድፍና በቀለማት ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• ከጨዋታው ያገኙትን ከ1-2 የሚደርሱ ጠቀሜታዎቻቸን ይገልፃሉ፡፡ | 2.2 ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎችዎች<br>*(6 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.2.1 ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎች<br>2.2.2 በንድፍ አስመስሎ መሥራት | • በአካባቢያቸው የሚዘወተሩ ወይም የሚያውቋቸው ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣<br>• ከዘረዘራቸው ውስጥ በይበልጥ ተማሪዎችን ሊመጥኑ የሚችሉትን በመምረጥና እንደባህሉ መሠረት ተማሪዎችን በፆታ በመክፈል እንዲጫወቷቸው ማድረግ፣<br>• ከጨዋታዎቹ በኋላ ለተማሪዎቹ ጥያቄ ማቅረብ፡፡ ለምሳሌ እነዚህ ጨዋታዎች መች ነው ሰዎች የሚጫወቱአቸው? የሚለብሱት ባህላዊ አልባሳት ምን ምን ናቸው ወዘተ.. ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡበት ማበረታታት፣<br>• ቀደም ሲል ያቀረቡትን ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎች እና ሌሎችንም በመጨመር ጨዋታዎቹን በቡድን በመከፋፈል ከባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎች ጋር የሚሄዱ አልባሳትንና የሙዚቃ መሣሪያዎች በአጨዋወቱ ውስጥ በማስገባት እንዲለማመዱ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• በቡድን የተለማመዱትን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡና አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች በባህላዊ አልባሳትና የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎችን ሲጫወቱ የሚያሳዩ ሥዕል እንዲስሉ የቤት ሥራ መስጠት፡፡ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ከሥራዎቹ መካከል የተሻለ የተሠራውን ሥራ በጋራ መምረጥ፡፡ |
| • ከ1-2 የሚሆኑ በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ ባህላዊ ጨዋታዎችንና ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ<br>• ከ1-2 የሚደርሱ የበዓላት ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡<br>• በበዓላት የባህል ጨዋታ ጊዜ ያለውን አለባበስ ይገልጻሉ፣ በተግባርም ለብሰው ያሳያሉ፣<br>• የጨዋታዎቹን እንቅስቃሴዎችና ባህላዊ አለባበስን በንድፍና በቀለማት ሠርተው ያሳያሉ፡፡ | 2.3 የበዓላት ባህላዊ ጨዋታ<br>*(6 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.3.1 በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ ባህላዊ ጨዋታዎች፣<br>2.3.2 ንድፍና ቀለም ቅብ | • በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ የባህላዊ ጨዋታዎች ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ ጨዋታዎቹም መች መችና እንዴት እንደሚጨፈሩ እንዲገልፁ ማድረግ፣<br>• በባህል ጨዋታዎች ጊዜ ስላለው አለባበስ የአልባሳት ቀለማት ወዘተ... ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>• የሚወዷቸውን የባህል የበዓላት ጨዋታዎች ከሙዚቃ ምት ጋር አቀናጅተው በቡድን እንዲጫወቱ ማድረግ፣<br>• ስለበዓላት የባህል ጨዋታዎች በቴፕሪኮርደር በማስደመጥ የጨዋታውን መልእክት እንዲገልጹ ማድረግ፣<br>• ባህላዊ ጨዋታዎችን ነፃ ሆነው በእንቅስቃሴ ምላሽ እንዲሠጡ ማድረግ፣<br>• ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የተለያዩ የበዓላት ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲለማመዱ ማድረግና የተለማመዱትን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ |

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| | | • የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎችን፣ በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ አልባሣትን የሚገልፁ ምሥሎችን በንድፍ በቀለማት እንዲሠሩ ማድረግ:: |
| • ከ1-2 የሚሆኑ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ከ1-2 የሚደርሱ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በንድፍና ቀለም ቅብ ይሠራሉ፣ | 2.4 ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>*(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.4.1 አካባቢ የሚታወቁ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>2.4.2 ንድፍና ቀለም ቅብ | • የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎችን፣ እና በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ አልባሣትን የሚገልፁ ምሥሎችን በንድፍና በቀለማት እንዲሠሩ ማድረግ::<br>• ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>• እያንዳንዱ መሣሪያ ለምንና መቸ እንደሚጠቅም መጠየቅና እንዲወያዩ ጊዜ መስጠት፣<br>• ቀላል ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በአካባቢ ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች ወይም ቁሳቁሶች እንዲሠሩ በቡድን የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• በሠሩት መሣሪያዎች ድምፅ እንዴት እንደሚፈጥሩ እንዴት መጫወት እንደሚችሉ ለክፍሉ እንዲያስረዱ ማድረግና ከተለያዩ መሣሪያዎች የሚወጡትን የተለያዩ ድምጾች በመጠቀም አንድ የተቀናጀ ድምፅ እንዲፈጥሩ ማበረታታት፣<br>• ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን እንዴት ጠብቀው ለትውልድ ማስተላለፍ እንዳለባቸው በቡድን ተወያይተው ለክፍሉ ተማሪዎች የደረሱበት ጭብጥ እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣<br>• ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችንና አልባሳትን በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • የባህላዊ ቅርሶች ምንነትና ጠቀሜታን በመዝመር ይገልፃሉ፣ | 2.5 የባህላዊ ቅርሶች ምንነትና ጠቀሜታ<br>*(5 ክፍለ ጊዜ)*<br>2.5.1 መዝሙር | • ተማሪዎች ባህላዊ ቅርስ ምን ማለት እንደሆነ፣ የሚሠጠው ጠቀሜታ፣ ምን ምን ቅርስ በአካባቢያቸው እንደሚገኝ ተወያይተው ምላሽ እንዲሠጡ ጥያቄዎችን ማቅረብ::<br>• ከተማሪዎች ሙከራ በኋላ ስለባህላዊ ቁሳቁሶች ምንነትና ጠቀሜታ ትርጉም ገለፃ ማድረግ::<br>• የእነዚህ ባህላዊ ቁሳቁሶች ጠቀሜታ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው እንዲዘምሩ ማድረግ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ከትምህርቱ ርዕሶች ጋር ተያይዥነት ያላቸው ሥዕሎችና ፎቶግራፎች
- ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች
- የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች
- ለንድፍና ቀለም ቅብ የሚያገለግሉ መሥሪያ መሣሪያዎች

## ክትትልና ግምገማ

- የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች መዘርዘር መቻላቸውን ለማረጋገጥ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣
- ባህላዊ ጨዋተዎቹን በነበረት መጫወታቸውንና አጨዋወታቸውን በንድፍና ቀለም ቅብ መግለጽ መቻላቸውን    በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎች እንቅስቃሴዎች ያገኙትን ጠቀሜታ መግለጻቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ የሠርግ ጨዋታ እንቅስቃሴዎችን፣ አልባሳትና የሙዚቃ መሣሪያዎች በንድፍና ቀለም ቅብ መግለጽ መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የበዓላት ባህላዊ ጨዋታዎችን ዓይነቶች መዘርዘር መቻላቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ከበዓላት ባህላዊ ጨዋታዎች አጨዋወት መደሰታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የባህላዊ ቅርሶች ምንነትና ጠቀሜታ በመዘመር መግለፃቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ምዕራፍ ሶስት፡- ጥንቃቄና ደህንነት፡- *(14 ክፍለ ጊዜ)*

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- ግቢንና ሠፈርን የማስዋብና የመንከባከብ ጠቀሜታን በመረዳት በተለያዩ መንገዶች ይገልፃሉ፣
- በእግረኛ መንገድ የማቋረጥና የድልድይ አጠቃቀም ክህሎትን በመዝመርና በተለያዩ ጨዋታዎች ይገልጻሉ፣
- የማግለልና መድሎ አስከፊነት በመገንዘብ ለኤች አይቪ/ኤድስ ህሙማን አስፈላጊውን እንክብካቤ የሚያደርጉበትን መንገድ ይገልፃሉ፡፡
- በራሳቸው መንገድ ስለጥንቃቄና ደህንነት በንድፍና ቀለም ቅብ ሰርተው ያሳያሉ፣

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፣*<br>• ግቢንና ሠፈርን በዕፅዋት የማስዋብ ከ1-2 ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ግቢንና ሠፈርን በዕፅዋት የማስዋብ ጥቅም ይዘረዝራሉ፣<br>• ግቢና ሠፈራቸውን ማስዋብ የሚሰጠውን ጥቅም የሚገልፁ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው ይዘምራሉ፣<br>• ከ1-2 የሚሆኑ የግቢና ሠፈር ንጽህና አጠ ባበቅን በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ፡፡ | 3.1 ግቢንና ሠፈርን በዕፅዋት ማሰዋብ *(5 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.1.2 መዝሙር፣<br>3.1.3 ንደፍና ቀለም ቅብ፣ | • ተማሪዎች የዕፅዋትን ጠቀሜታና እንክብካቤ አስመልክቶ ካለፉት ክፍሎች በተሻለ ሁኔታ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣<br>• ግቢንና ሠፈርን በዕፅዋት ማስዋብ ያለውን ጠቀሜታ እንዲገልጹ በቡድን ሥራ መስጠት፣<br>• በዕፅዋት ግቢንና ሠፈርን የማስዋብ መዝሙር እየዘመሩ እንዲቀሳቀሱ ማድረግ፣<br>ምሳሌ፡– ዕፅዋት እተክላለሁ፣<br>ግቢንና ሠፈርን አስውባለሁ፡<br>ዕፅዋትን ያልተከለ አገሩን ለድርቅ አጋለጠ፡፡<br>• ጥሩና ማራኪ ቦታዎች ናቸው የሚባሉትን ሠፈርን በጉብኝት መልክ እንዲመለከቷቸው ማድረግ፣<br>• በመቀጠል በቡድን ያዩትን እንዲገልጹ ዕድል መስጠት፣<br>• ስለደን ጭፍጨፋና በዚህ ሳቢያ የሚመጡትን ችግሮች የሚያወሳ ምሳሌ ራሳቸው ፈጥረው መጀመሪያ በንድፍ ቀጥሎ ቀለም በመቀባት እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• በተቃራኒው በዕፅዋት ያማረ ግቢና ሠፈር ምሥል ራሳቸው በሀሳብ ፈጥረው ወይም ፎቶግራፎችን በማሣየት ሥዕል እንዲስሉ ማበረታታት፡፡ |
| • ከ1-2 የሚሆኑ ስለመንገድ ማቋረጥና ድልድይ አጠቃቀም መደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ይገልጻሉ፣<br>• ስለመንገድ ትራፊክ ደህንነት የሚገልጹ መዝሙሮች፣ ግጥሞችንና ዜማ አስተውለው ይዘምራሉ፣<br>• ስለመንገድ ማቋረጥና ድልድይ አጠቃቀም የሚገልጹ ደህንነት የሚገልፁ ጥቃቅትን ጨዋታዎችን ይጫወታሉ | 3.2 መንገድ ማቋረጥና የድልድይ አጠቃቀም *(5 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.2.1 መዝሙር፣<br>3.2.2 ጨዋታ | • መንገድ በጥንቃቄ ማቋረጥና ወንዝ መሻገር፣ ከጥንቃቄ ጉድለት ሊደርሱ ስለሚችሉ አደጋዎች ቀደም ብለው የተማሩትን ለማስታወስ ጥያቄዎችን መጠየቅና ማወያየት<br>• በውይይት ላይ ከሚሠጡት ሀሳቦች በመነሣት ስለመኪና መንገድ አጠቃቀም፣ እንዲሁም ወንዝ በጥንቃቄ የመሻገር ዘዴዎችን አጭር መግለጫ በመስጠት ትምህርቱን ማጠ ናከር፣<br>• እነዚህ ርዕሶች የሚቀርቡት ተነጣጥለው በየተራ ነው፡፡<br>• የመኪና መንገድን በጥንቃቄ ማቋረጥና ወንዝ መሻገርን አስመልክቶ አጫጭር ግጥሞችን እንዲያዘጋጁ የቤት ሥራ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • ስለ ትክክለኛ መንገድ ማቋረጥና ድልድይ አጠቃቀም የሚያሳዩ ከ1-2 የሚሆኑ ሥዕሎችን ይስላሉ፣ | 3.2.3 ንድፍና ቀለም ቅብ | መስጠት፣<br>• ከተዘጋጁት ግጥሞች የተሻሉትን እንዲመርጡ በማድረግ ዜማ በጋራ መፍጠርና መዝሙሮችን አዘጋጅቶ እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• ቀደም ብሎ ተዘጋጅተው በመማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፍት የተካተቱ መዝሙሮቹን ግጥሞችን ዜማቸውን በማጥናት እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• በተለያየ ቡድን ሆነው የተለያዩ መዝሙሮች ላይ አጥንተው እንዲዘጋጁና ለክፍሉ ተማሪዎች በመዝሙር ውድድር ላይ እንዲያቀርቡ ማመቻቸት፣<br>• ሁለት ርዕሶችን "የትራፊክ ደህንነት" እና "ወንዝ በጥንቃቄ መሻገር" የሚሉትን በማቅረብ እያንዳንዳቸው ተማሪዎች የፈለጉትን ወስደው በሥሩ የመጡላቸውን ሀሳቦች እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>ለምሣሌ፡ " የትራፊክ ደህንነት" የሚለውን ርዕስ የመረጡት ተማሪዎች ሊዘረዝሩ የሚችሉት፡<br>- በእግርኛ ማቋረጫ መንገድ ላይ መንገድ ማቋረጥ፣<br>- ግራና ቀኝ መመልከት<br>- መብራት መመልከት<br>- ሁልጊዜ በግራ በኩል መንገድ ይዞ መሄድ ወዘተ.<br>• በመረጡት ርዕስ ሥር የዘረዘሩትን ሀሳቦች እንዲያስረዱ ማድረግ፣<br>• ሀሣባቸውን በንድፍ ሥራ ሠርተው እንዲያቀርቡ አስፈላጊ መሣሪያዎችን ማለትም እርሣስ፣ ወረቀት፣ ቀለሞችን እንዲያዘጋጁ ማመቻቸት<br>• የንድፍ ሥራ ሠርተውና የተዘጋጁትን ቀለሞች ተጠ ቅመው በመቀባት ሀሣባቸውን በሥዕል እንዲገልፁ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• ሠርተው ባቀረቡት ላይ መግለጫ እንዲሠጡበት በማድረግ በክፍሉ ተሣትፎ አወዳድሮ የተሻሉትን በቁጥር መውሰድና በተማሪዎች እንዲጐበኙ የሚታይ ቦታ ላይ መሰቀል፡፡ |
| • በኤች አይቪ ኤድስ ለተያዙት እንክብካቤና ድጋፍ በመስጠት ማግለልና መድሎ የሚወገዱበትን ከ1-2 ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 3.3 ኤች አይቪ ኤድስ *(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.3.1 ማግለልና መድልዎን ማስወገድ<br>3.3.2 መዝሙሮች፣<br>3.3.3 የንድፍና ቀለም ቅብ | • በኤች አይቪ/ኤድስ የተያዙ ወገኖችን ማግለልና መድልዎ ማድረግ በሚያስከትለው ችግር ላይ እንዲወያዩ ማድረግና በውይይቱ ለችግሮቹ የመፍትሔ ሀሳቦችን እንዲያስቀምጡ ማድረግ፣ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • በኤች አይቪ/ኤድስ የተጐዱ ህሙማን መገለል እንደሌለባቸው የሚገልጽ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ይዘምራሉ፣<br>• ህሙማን እንክብካቤና ድጋፍ አጥተው ሲገለሉ የሚያሳይ ከ1-2 ሥዕል በመሥራት የማግለልና መድልዎን አስከፊነት ይገልፃሉ፣ | | • በኤች አይቪ/ኤድስ የተያዙእንክብካቤ አለማድረግና ማግለል በህሙማኑ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ከነቤተሰቦቻቸውና ከጤና ባለሙያዎች ጋር በመወያየት ሀሳቦችን ይዘው እንዲመጡ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• በኤች አይቪ/ኤድስ የተያዙ እንክብካቤ ማድረግ እንደሚገባና አለማግለል የሚያንፀባርቁ መዝሙሮች ማዘመር፣<br>• በኤች አይቪ/ኤድስ የተያዙ በመጀመሪያ መዝሙሩን እንዲያጠኑት ማድረግና ከተገቢ እንቅስቃሴዎች ጋር በማቀናጀት እንዲዘምሩ ማድረግ፡፡ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ከትምህርት ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥዕሎች፣ ፓስተሮችና ፎቶግራፎች፣
- ለንድፍና ቀለም ቅብ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣
- ከበሮ፣ ሪትምስቲክ፣ ፅናፅል፣

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ግቢንና ሠፈርን በዕፅዋት ለማስዋብ መነሳሳታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ስለኤች አይቪ/ኤድስ የሚገልጽ መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ስለኤች አይቪ/ኤድስ በዕፅዋት የተዋበ ግቢንና ሠፈርን ምሥል መሳላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በመንገድ ማቋረጥና ድልድይ አጠቃቀም ጊዜ መደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣
- የእግረኛ መንገድ ማቋረጥን የሚገልጹ ጨዋታዎች መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በኤች አይ- ቪ የተያዙ የማግለልና መድልዎ አስከፊነት መግለጽ መቻላቸውን ለማረጋገጥ በቃል ወይም በጽሑፍ ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- በኤች አይቪ/ኤድስ የተያዙ ማግለልና መድልዎን የሚያወግዙ መዝሙር ከእንቅስቃሰዎች ጋር አቀናጅተው መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በኤች አይቪ/ኤድስ የተያዙ መገለልና ድጋፍ ማጣትን የሚያሳዩ ሥዕል መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፡፡

## ምዕራፍ አራት፡- የሰውነት ክፍሎች ተግባራት *(54 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** *ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- *መሠረታዊ የእንቅስቃሴ ክህሎትን በማዳበር በእጅና በእግር የሚከናወኑ ተግባራትን ይሠራሉ፣*
- *የተለያዩ ሪትሞችንና እንቅስቃሴዎችን በመገንዘብ አቀናጅተው ያከውናሉ፣*
- *የእንቅስቃሴዎችን ጠቀሜታ ተረድተው በራሳቸው መንገድ በንድፍና ቀለም ቅብ፣ ጨዋታና መዝሙር ይገልፃሉ፣*

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፣*<br>• ከእጅ ተግባራት ጋር የተያያዙ ከ2-3 ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፣<br>• ጭብጨባን ከሚያዳምጡት ሙዚቃ ምት ጋር ጊዜ ጠብቀው በማቀናጀት ይጫወታሉ፣ | **4.1 በእጅ የሚከናወኑ ተግባራት**<br>*(9 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.1.1 ከእጅ ተግባራት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች<br>4.1.2 ጣቶችን በማፋተግና በእጅ በማጨብጨብ የሚወጡ ድምፆች | • አውራ ጣትና የመሐል ጣትን በማፋተግ ድምፅ ለማውጣት እንዲሞክሩ አጭር ጊዜ መስጠትና አንዱ የሌላውን እንዲያዳምጥና እንዲያስተካክል ማድረግ፣<br>• ከብዙ ልምምድ በኋላ በሚገባ ድምፅ መፍጠር ሲችሉ የተለያዩ ምቶችን በማሣየት ተከትለው እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• በጭብጨባና በጣቶች ድምፅ ፈጥረው በማዋሀድ የተለያዩ ሪትሞችን እንዲጫወቱ የቡድን ሥራ መስጠትና ተለማምደው ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>• ሙዚቃ ማሰማትና በጭብጨባና በጣት የሙዚቃውን ምትን ተከትለው እንዲያጅቡ ማድረግ፣<br>• በጭብጨባ፣ በጣትና በእግር ምቶች የሚወጡትን ድምፆች በማዋሀድ ትርጉም ያለው ሪትም እንዲፈጥሩ ማለማመድ<br>• ተማሪዎቹን በቡድን መከፋፈልና እያንዳንዱ ቡድን ተለማምዶ በጭብጨባ በጣት በእግር የሚወጡ ድምፆችን በማቀናበር ሪትም በመጫወት ውድድር እንዲያካሂዱ ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ |
| • ከሰውነት ተግባራት ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎችን በኮላዥ በራሳቸው መንገድ ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• የሠሩትን ሥራዎች የአሠራር ሂደት ይገልፃሉ፣<br>• ጠቃሚ የሆኑ ግብረመልሶችን በመቀበል የተሻለ ሥራ ሠርተው ያቀርባሉ፣ | 4.1.4 ኮላዥ | • ቀደም ተብሎ በኮላዥ ተሠርተው የተዘጋጁ የተለያዩ ምሥሎችን ማቅረብና እንዲያዩት፣ እንዲነኩት አሠራሩን እንዲገነዘቡ እንዲወያዩበት ማድረግ፣<br>• ከተመለከቱት በመነሣት ራሣቸው ተመሣሣዩን መሥራት ይችሉ እንደሆንና እንዴት ሊሠሩ እንደሚችሉ መጠየቅና አሠራሩን ከውስጣቸው እንዲያወጡ ማድረግ፣<br>• ስለአሠራሩ ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት ማስረዳት፣<br>• በቅድሚያ የተለያዩ ርዕሶች ላይ የንድፍ ሥራ እንዲሠሩና ወረቀት ቆራርጠው በመለጠፍ በኮላዥ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | • የፕሮጀክት ሥራ መሥጠትና በመጨረሻ አወዳድሮ የተሻሉትን በመወሰድ ለእይታ ማቅረብ፣ |
| • የመንጠር ምትን በቀላል የምት መሣሪያዎች በመታገዝ አዋህደው በመጫወት ተግባሮአቸውን ያሳያሉ፣<br>• አጨዋወቶችን በራሳቸው መንገድ በሥዕል ይገልሉ፣ | **4.2 እጅና እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራት***(3 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.2.1 የመንጠር ምት | • የክፍሉን ተማሪዎች እንደብዛታቸው መሠረት በረድፍ ማቆም ከዚያም ባሉበት የመንጠር እንቅስቃሴዎችን እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ከላይ ያለውን እንቅስቃሴ በጭብጨባ ምት ማጀብ፣<br>• ረድፉ እንደተጠበቀ እስከ 10 ሜትር ድረስ በጭብጨባ፣ በፊሽካና በከበሮ ምት የመንጠር እቅስቃሴን ማሠራት፣<br>• የጭብጨባውን ምት ፍጥነት በመጨመር ማሠራት፣<br>• ለቡድኖቹ የመነሻ መሥመር ማዘጋጀትና ከመነሻው መሥመር 10 ሜትር ርቀት ላይ ምልክት ማድረግ፣ ከዚያም ከመነሻው መሥመር ኋላ እንዲቆሙ ማድረግና ተዘጋጅ፣ ሂድ የሚል ምልክት ሲሰጥ የ10 ሜትር ደርሶ መልስ በመሣሪያዎቹ ምት ወይም ያለምት በፍጥነት በመሮጥ እንቅስቃሴውን ቀድሞ እንዲጨርሱ በማድረግ በመካከላቸው ውድድር መፍጠር፣<br>• እንቅስቃሴዎቹን በገባቸው መሠረት መጀመሪያ ንድፍ እንዲነድፉ ቀጥሎ ንድፉን ቀለም እንዲቀቡ በማድረግ እንቅስቃሴዎቹን በሥዕል እንዲገልጹ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• ስለሠሯቸው ሥራዎች እንዲገልጹ ማድረግና ከእያንዳንዱ ገለፃ በኋላ ከተሠሩት ሥራዎች መካከል የተሻለው ሥራ በጋራ መምረጥና በሚታይበት ላይ መስቀል፣ |
| • ከ8-10 ጊዜ ኳስ ከወርውሩ ካጨበጨቡ በኋላ ይቀልባሉ፣<br>• ለመወርወርና መቅለብ የሚጠቅሙ መሠረታዊ የሰውነት አቋቋምን ይገልጻሉ፣<br>• ከመወርወርና መቅለብ ጋር የተያያዙ የክንዋኔ ትዕይነቶችን በራሳቸው መንገድ በንድፍና ቀለም ቅብ ያሳያሉ፣ | 4.2.2 ኳስ ወርውሮ መቅለብ<br>*(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>• ኳስ ወርውሮ መጨብጨብና መቅለብ | • ተማሪዎች በአንደኛ እና ሁለተኛ ክፍል የባቄላ ከረጢት ወርውሮ መቅለብ የጨርቅ ኳስ ወርውሮ መቅለብን ተምረውታል። ይህንኑ በማስታወስ ሜዳ ውስጥ በተንተን ብለው ተራ በተራ የባቄላ ከረጢትን የጨርቅ ኳስ ወርውረው እንዲቀልቡ ማድረግ፣<br>• ስለመወርወርና መቅለብ የሚያውቁትንና የተረዱትን እንዲገልጹ መጠየቅ፣<br>• በመቀጠል ኳስ ወርውሮ ማጨብጨብ መቅልብን በተግባር ሠርቶ ማሣየትና አሠራሩንና መሠረታዊ የሰውነት ሁኔታ መግለጽ፣<br>• በገለፃውና ባዩት መሠረት በግል ኳስ ከራስ በላይ ወረውሮ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | አጨብጭቦ መቅለብን እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• በጥንድ በመሆን ወርውሮ አጨብጭቦ መቅለብን ማሠራት፣<br>• ሦስት ሦስት በመሆን በመካከላቸው ያለውን ርቀት በመጨመር ኳስ ወርውሮ አጨብጭቦ መቅለብን ማሠራት፣<br>• በግል ኳስ ወደፊትና ወደላይ ወርውሮ ደርሶ አጨብጭቦ መቅለብን ማሠራት፣<br>• ቀስ በቀስ በተከታታይ የሚወረወሩትን ቁጥሩን በመጨወርና በመካከላቸው ውድድር በመፍጠር እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• የተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ምሥል በራሳቸው መንገድ በንድፍና በቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የሠሩትን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩና አስተያየት እንዳሰጥበት ማድረግ፣ |
| • በጥንድ ሆነው ገመድ ዝላይን ከመዝሙር ጋር በማቀናጀት ይዘላሉ፣<br>• የገመድ ዝላይ የአሠራር ሂደት ቅደም ተከተል ይገልጻሉ፣<br>• እንቅስቃሴዎቹን የሚገልጽ ምሥል በንድፍና ቀለም ቅብ ይሠራሉ፣ | 4.2.3 ገመድ ዝላይ *(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>• በጥንድ የገመድ ዝላይ | • ተማሪዎች በአንደኛና ሁለተኛ ክፍል በቦታ ላይ ገመድ ዝላይ እና በእንቅስቃሴ የገመድ ዝላይ ተምረዋል። ያንኑ በማስታወስ የተወሰነ ጊዜ ወስደው ሁለቱን እንቅስቃሴዎች ተራ በተራ እንዲሠሩ በቂ ጊዜ መስጠት፣<br>• በጥንድ በመሆን በአንድ ገመድ ለሁለት እንዲዘሉ ማድረግ። የጊዜውን መጠን እንደተማሪዎቹ የአካል ብቃት ደረጃ መወሰን፣<br>• ሁሉም ተማሪዎች እንዲሞክሯቸው በማድረግ በተሻለ ቅንጅት የሚሠሩ ተማሪዎችን በመለየት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ እና ለሌሎችም ትክክለኛውን አሠራር ተከትለው እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የተማሪዎችን እንቅስቃሴ እየዞሩ በመከታተል እርምትና ድጋፍ መስጠት፣<br>• በእንቅስቃሴዎቹ መካከል ለተማሪዎች እረፍት ለመስጠት ይቻል ዘንድ የተወሰኑትን ሲሠሩ ሌሎች ደግሞ እንቅስቃሴዎቹን በመዝሙር እያጨበጨቡና እያሸበሸቡ ከእንቅስቃሴው ጋር በሚስማማ ቅንጅት እንዲያጅቧቸው እና ሌሎችም ተራቸውን ጠብቀው እንዲሠሩት ማድረግ፣<br>• ይንኑ እንቅስቃሴ እቤታቸው ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር እንዲሠሩ የቤት ሥራ መስጠት፣<br>• በይዘቱ የተመረጡትን እንቅስቃሴዎች በንድፍና ቀለም ቅብ ማሠራት፣ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | • የተሻሉ ሥራዎችን በጋራ በመምረጥ ለሁሉም በሚታይ ቦታ መለጠፍ፣ |
| • በቦታ ወደጐን በመሽከርከር ሚዛናቸውን ይጠብቃሉ፣<br>• እንቅስቃሴዎቹን በንድፍና ቀለም ቅብ ይገልጻሉ፣ | 4.2.4 መሽከርከር *(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.2.1 መሽከርከር<br>• በቦታ<br>• ወደጐን | • ተማሪዎች በሜዳው ውስጥ በተንተን ብለውና ሊያሠራቸው የሚችል ቦታ ይዘው በቦታ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ እና ከቀኝ ወደግራ ተራ በተራ ነፃ ሆነው እንዲሽከረከሩ እድል መስጠት፣<br>• የተማሪዎችን ሙከራ እየተዘዋወሩ መመልከትና የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉትን በመለየት ለሌሎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ሌሎችም ባዩትና በተረዱት መሠረት ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲሠሩ በቂ ጊዜ ጊዜ መስጠት፣<br>• በመቀጠል ስለ እንቅስቃሴው አሠራር ገለፃ ማድረግና በተግባርም ሠርቶ ማሣየት፣<br>• በገለፃው መሠረት ቀስ በቀስ እንቅስቃሴውን በማሳደግ አንድ ሙሉ ዙር ወይም $360^0$ መሽከርከር እስከሚችሉ ድረስ ማሠራት። በዚሁ መሠረት<br>- እጆችን ወደጐን በመዘርጋት $90^0$ መዞርን ማሠራት፣<br>- እጆችን ወደጐን በመዘርጋት $180^0$ መዞርን ማሠራት፣<br>- እጆችን ወደጐን በመዘርጋት $360^0$ መዞርን ማሠራት፣<br>• በቦታ የመሽከርከር እንቅስቃሴን በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲገልጹ የቤት ሥራ/የክፍል ሥራ መስጠት የተሠሩትን ሥራዎች በማረም በትክክል መሥራታቸው ማረጋገጥ፣ |
| • በሆድ ተኝቶ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ማንሳት፣ ሚዛናቸውን ይጠብቃሉ፣<br>• የእንቅስቃሴውን አሠራር ይገልጻሉ፣<br>• በሆድ ተኝቶ እጆችንና እግሮችን የማንሣት እንቅስቃሴን በሥዕል ሠርተው ያሳያሉ፣ | 4.2.5 ሚዛን መጠበቅ *(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>• በሆድ ተኝቶ እጆችንና እግሮችን ማንሳት፣ | • ወደ ዋናው የትምህርት ርዕስ ከመገባቱ በፊት ተማሪዎች በ2ኛ ክፍል የተማሩትን ማለትም በሁለት እግር ዘሎ በሁለት እግር ማረፍን በአንድ እግር ቆሞ እጆችን ወደተለያየ አቅጣጫ መዘርጋትን በቂ ጊዜ ወስዶ ማሠራትን መከለስ፣<br>• በመቀጠል ስለ እንቅስቃሴው አሠራርና ጠቀሜታ መግለጽ፣<br>• በሆድ ተኝቶ እግሮች ከመሬት ሳይነሱ እጆችን በማንሳት ሚዛን መጠበቅን ማሠራት፣<br>• በሆድ ተኝቶ እጆች ከመሬት ሳይነሱ እግሮችን ከመሬት በማንሣት ሚዛን መጠበቀን ማሠራት፣ |

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘቶች* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| | | • እጆችንና እግሮችን በማንሳት ሚዛን መጠበቅን ማሠራት፣<br>• ተማሪዎች እንቅስቃሴውን ሲሠሩ እየዞሩ በመመልከት አስፈላጊውን እርምት ማድረግ፣<br>• በተደረገው ምልከታ የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉትን ተማሪዎች በመምረጥ ለሁሉም ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• የተቀሩትም ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ያዩትን የአሠራር ቅደም ተከተል መሠረት በማደረግ ከበፊቱ አሻሽለው እንዲሠሩ ማበረታታት፣<br>• በተግባር የተማሩትን በሥዕል እንዲገልጹ ማድረግ፣ |
| • ኳስ በእጅ/በእግር መትተው መልሰው ይይዛሉ/ያቆማሉ፣<br>• የእያንዳንዱ አሠራር ቅደም ተከተል ይገልጻሉ፣<br>• ተግባራዊ እንቅስቃሴውን በንድፍና ቀለም ቅብ ይገልጻሉ | 4.2.6 *መምታትና ማቆም (7 ክፍለ ጊዜ)*<br>• *ኳስ መምታትና ማቆም* | • ተማሪዎች በ2ኛ ክፍል ኳስ መቀባበልን ተምረዋል። ይህንኑ በማስታወስ ነፃ ሆነው ኳስ መቀባበልን እንዲሠሩ በቂ ጊዜ መመደብ<br>• እያንዳንዱ ተማሪ አንድ አንድ ኳስ እንዲኖራቸው ማድረግና በማይጋጩት ሁኔታ ሰፊ ቦታ ይዘው ኳስ ከራስ በላይ እየወረወሩ እንዲቀልቡ ማድረግ፣<br>• ኳስ እየወረወሩ መቅለቡን ከእንቀስቃሴ ጋር እንዲሠሩ በቂ ጊዜ መስጠት፣<br>• የመወርወርና መቅለብ መሠረታዊ የሰውነት አቋቋም መግለጽና በተግባርም ሠርቶ ማሣየት፣<br>• ተማሪዎችን በጥንድ በማቆም ነፃ ሆነው ኳስ መምታትና ማቆምን በራሳቸው መንገድ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ከተማሪዎች ነፃ ሙከራ በኋላ ኳስ እንዴት መምታትና ማቆም እንዲሚቻል ገለፃ ማድረግና ሠርቶ ማሣየት፣<br>• የክፍሉን ተማሪዎች ደረጃ የሚመጥንና በልዩ ልዩ ክንውኖች አማካይነት ደጋግመው እንዲሠሩትና እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• የመምታታትና ማቆም ተግባራዊ እንቅስቃሴን የሚያጠናክሩ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች ፈልጐማጫወት፣<br>• እንቅስቃሴውን በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲገልጹ በቡድን ሥራ መስጠት። የተሠራውን ሥራ እንያንዳንዱ ቡድን እንዲገልጽ ማድረግ፣ |
| • ሙዚቃ በመስማት በራሳቸው መንገድ ነፃ እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ፣<br>• ከሪትሚካዊ ጋር ተግባራትን በራሳቸው | **4.3 ሪትሚካዊ እንቅስቃሴዎች**<br>*(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.3.1 በሙዚቃ ምት ነፃ እንቅስቃሴዎች | • ልዩ ልዩ የምት መሣሪያዎችን በመጠቀምና ተማሪዎቹን እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ማለማመድ፣<br>• የሙዚቃ ምትን ተከትሎ ፍጥነት በመቀያየር እንዴት |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| መንገድ እንቅስቃሴዎች በንድፍና ቀለም ቅብ ይሠራሉ፣ | | መንቀሳቀስ እንደሚቻል ሠርቶ ማሣየት፣<br>• ከገለፃው በኋላ ሠርተው እንዲያሳዩ መጠየቅና የተሻለ የሠሩትን በመምረጥ ለሌሎች ጓደኞቻቸው እንዴት እንደሚሠራ እንዲያሳዩ ማድረግና በዚሁ መሠረት እንቅስቃሴውን እየሠሩ እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• ተስማሚውን ዜማ በመምረጥ ተማሪዎች እንዲሰሙ ወይም እንዲጫወቱ ማድረግ፣<br>• ዜማውን ከሰሙ ወይም የተወሰኑ ተማሪዎች ከተጫወቱት በኋላ እንቅስቃሴውን በቡድን ተከፋፍለው በራሳቸው መንገድ ከዜማው ጋር እንዲያቀናጁት ማድረግ፣<br>• እያንዳንዱ ቡድን የሠራውን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡና አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ፣<br>• መጨረሻም እንቅስቃሴዎቹን በሥዕል እንዲገልጹ ማድረግ። |

## *የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-*

- *የተለያዩ መጠን ያላቸው ኳሶች*
- *ለኮላዥ ሥራ የሚያገለግሉ የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችና ቁሳቁሶች*
- *የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች/ፊሽካ፣ ከበሮ፣ ሪትምስትክ/*
- *የመዝለያ ገመዶች*
- *ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥዕሎች*
- *ኳሶች*
- *ቴፕሪኮደር*
- *ልዩ ልዩ የሙዚቃ ምት መሣሪያዎች፣*

## *ክትትልና ግምገማ፡-*

- *በእጅ የሚከናወኑ ጨዋታዎችን መዘርዘር መቻላቸውን ለማረጋገጥ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣*
- *ከልዩ ልዩ ነገሮች ኮላዥ መሥራት መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *እጅና እግርን በማቀናጀት የተለያዩ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን መሥራት መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *ኳስ ወርውሮ በማጨበጨብና በመቅለብ ጊዜ መሠረታዊ የሰውነት አቋቋም እንዴት እንደሆነ እንዲገልጹ የቃል /የጽሑፍ ጥያቄ መጠየቅ፣*
- *እንቅስቃሴዎቹን ከመዝሙር ዜማ ጋር አቀናጅተው መሠራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *እንቅስቃሴዎቹን የሚገልጹ ሥዕል መሥራታቸውን የቤት ሥራና የፕሮጀክት ሥራ በመስጠት ማረጋገጥ፣*
- *እንቅስቃሴዎችን ከሙዚቃ ምት ጋር አቀናጅተው መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *የንድፍና ቅብ ሥራ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣*

# የሥነ-ጥበብና ሰውነት ማጐልመሻ
# ትምህርት ሲለበስ

# 4ኛ ክፍል

## ምዕራፍ አንድ፡- በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች *(41 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- የተፈጥሮን ውበት በማድነቅ አካባቢያቸውን ይነከባከባሉ፣
- ባህላቸውንና ባህላዊ ቅርሶችን ጠቀሜታ በመገነዘብ ባህላቸውንና ቅርሶቻቸውን ይጠብቃሉ፣
- ስለአካባቢያቸው መልከ ዓምድር ያላቸውን አድናቆት በንድፍና በመዝሙር በመግለፅ ያሳያሉ፣
- ባህልና ቅርስ የመጠበቅን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች፡-*<br>• የአካባቢያቸውን መልክዓምድር በሥዕል ይገልፃሉ፣<br>• የሠሩትን መልክአምድር አግባብነት ያለውን ቀለማት በመጠቀም ይቀባሉ፣<br>• ስለለአካባቢያቸው መልክዓምድር የተፈጥሮ ውበት የሚገልፁ መዝሙር ይዘምራሉ፣<br>• ስለትምህርታዊና አዝናኝ ጉዞ ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣ | **1.1 በአካባቢ የሚገኝ መልከዓምድር**<br>*(14 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.1.1የአካባቢ መልክአምድር<br>• ቅርጽ<br>• ቀለም<br>1.1.2መዝሙር<br>1.1.3ንድፍና ቀለም ቅብ | • የአካባቢን መልክዓምድር በግልፅ ሊያሳይ የሚችል ቦታ ተማሪዎችን መውሰድ፣<br>• ስለትምህርታዊና አዝናኝ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ጠቀሜታ ማስረዳት፣<br>• በጉዞ ላይ እያሉም ሆነ ወደሚፈለግበት ከደረሱ በኋላ የሚመለከቷቸውን ነገሮች እንዲዘረዝሩ የተለያዩ ጥያቄዎችንም መጠየቅ፣<br>• ስለአካባቢው ተፈጥሮ ሜዳ፣ ጋራ፣ ደን፣ አእዋፋት፣ ዕፅዋት የተለያዩ ጥያቄዎችን ተራ በተራ በማንሣት እያስተዋሉ እንዲመልሱ ማድረግ፣<br>• የአካባቢ መልከዓ ምድር በሚል ርዕስ የተመለከቱትንና ያስተዋሉትን በንድፍ እንዲሠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣<br>• ባስተዋሉት መሠረት የሠሩትን ንድፍ ተስማሚ ቀለሞችን እንዲቀቡና እንዲያስውቡ ማድረግ፣<br>• ሥዕሎቹን ተራ በተራ ለክፍሉ ተማሪዎች ማቅረብና የተሻለውን በጋራ እንዲመርጡ ማበረታታት፣<br>• ስለአካባቢ መልክዓምድር ውበት፣ ልምላሜ፣ ተፈጥሮ የሚገልፁ መዝሙሮችን እንዲያዘጋጁ በቡድን ከፍሎ ኋላፊነት መስጠት፣<br>• በየቡድኑ አዘጋጅተው ያመጡትን በጋራ እንዲዘምሩ ማድረግና የተሻሉትን መምረጥና ማለማመድ፣ |
| • የአእዋፋትን ውበት ቀለምና ተፈጥሮ በሥዕል ይገልፃሉ፣<br>• የአዕዋፋትን ተፈጥሮአዊ ቀለም በመለየት ከቅጠላ ቅጠልና ከአፈር ተስማሚ ቀለሞችን ያዘጋጃሉ፣<br>• የአእዋፋትን ድምፅና እንቀስቃሴ | **1.2 በበአካባቢ የሚገኙ አዕዋፋት**<br>*(13 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.2.1 በአካባቢው የሚገኙ አዕዋፍ ድምፅ እንቅስቃሴና ምስልን አስመስሎ መሥራት፣ | • በአካባቢ የሚገኙ አዕዋፋትን በአይነት በቀለምና በመጠናቸው ያውቋቸው እንደሆነ፣ የትኞቹን እንደሚወዱ ወዘተ... ጥያቄዎችን መጠየቅና አስተያየታቸውን ማዳመጥ፣<br>• የትምህርታዊ ጉዞ ዝግጅት ማድረግና ለእይታ አመቺ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| አስመሰለው ይሠራሉ፣ | | የሆነበት ቦታ ጊዜ ተማሪዎችን መውሰድ፣<br>• በጉዞ ላይም ሆነ ቦታው ላይ ሲደርሱ የሚያዩዋቸውን ወፎች ዓይነት፣ ቀለማቸውን መጠናቸውን እንዲያስተውሉና በውይይት ካነሱት ጋር እንዲያነፃፅሩ ማድረግ፣<br>• ከደረሱበት አካባቢ ለቀለማት ማዘጋጃ የሚረዱ ቅጠላ ቅጠሎችን አፈር ወዘተ... እንዲይዙ ማድረግ፣<br>• የተለያዩ አዕዋፋት በሚል ርዕስ ያስተዋሏቸውን በንድፍ እንዲሠሩ ማበረታታት፣<br>• የተለያዩ አእዋፋትን በመምረጥ የእነሱን ድግምዕና እንቅስቃሴ አስመስለው እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የሠሯቸውን ንድፎች በቀለማት /ያዘጋጇቸው ሊሆኑ ይችላሉ/እንዲያስውቧቸው ማድረግ፣<br>• ከሠሯቸው ሥዕሎች ውስጥ የተሻሉትን እንዲመርጡ በማድረግ ለእይታ ማቅረብ፣<br>• ከአእዋፋት ጋር የተያያዙ ግጥምና ዜማ በቡድን በመሆን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>• ስለአእዋፋት የተመረጡትን መዝሙሮች አጥንተው እንዲዘምሩና ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ |
| • በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች ለተለያዩ ተግባራት መዋል እንደሚችሉ ይገልጻሉ፣<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮች ተጠቅመው የተለያዩ ለኤስቴቲክስ ማስተማሪያ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ይሠራሉ፣ | 1.1.3 **በአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን መጠቀም** *(14 ክፍለ ጊዜ)*<br>1.3.1 ለኤስቴቲክስ ማስተማሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት<br>• ሪትም ስቲክ<br>• ዋሽንት<br>• ከበሮ<br>• ክራር<br>• የተለያዩ ዲዛይኖች ሞዴል የቤት፣ የመኪና፣ የብስክሌት ወዘተ... | • ከአካባቢው ቁሳቁሶችን ተጠቅመው የተለያዩ ነገሮችን መሥራት እንደሚቻል በመግለጽ ያላቸውን ተሞክሮ እንዲገልጹ እድል መስጠት፣<br>• በሸቦ፣ ክር፣ ክርታስ፣ ወዘተ.. ተጠቅመው የዋሽንትና የከበሮ ሞዴል እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣<br>• የተለያዩ ቀላል የስፖርትና የሥነ-ጥበብ መገልገያ መሣሪያዎችን እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣<br>• በአካባቢ መሣሪያዎች የሠሯቸውን ነገሮች ለተግባር ሥራቸው እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ከአካባቢ የሚገኙ ጠቃሚ ቁሳቁሶች፣
- የንድፍ መሣሪያዎች/እርሳስ፣ ቻርኮል፣ ፔንስል፣ ውሃ ቀለም፣ ከለር እርሳስ ወዘተ/
- ለኤስቴቲክስ መሥሪያ ተግባራት የሚያገለልሉ ቁሳቁሶች
- የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች

## ክትትልና ግምገማ፡-

- የተፈጥሮን ወብት በሙዚቃና በሥዕል ማድንቃቸውንና መንከባከባቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ስለቀለማት ያላቸውን ግንዛቤ  ለማወቅ የሠሩትን መልከዓምድርና አዕዋፋትን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ስለአካባቢ መልከዓ ምድርና አእዋፋት ያላቸውን ስሜት አውጥተው በንድፍ መግለፅ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የስዕል ፕሮጀክት ሥራዎችን በግልና በቡድን በመሥጠት ሥራዎቻቸውን መገምገም፣

## ምዕራፍ ሁለት፡- ባህልና ቅርስ *(27 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-

- የልጆች ባህላዊ ጨዋታ አይነቶችን ተገንዝበው በጨዋታ ይገልፃሉ፣
- ባህልንና ባህላዊ ቅርሶችን ጠቀሜታ በመገንዘብ ይንከባከባሉ፣
- የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችና ጭፈራዎችን በመጫወት ያሳያሉ፣
- የአካባቢን ባህል የሚያንፀባርቁ ሀሣቦችን በሥነ ጥበብ በመግለፅ ያሳያሉ፣

| ***አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ*** | ***ይዘት*** | ***የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች*** |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• የልጆችን ባህላዊ ጨዋታዎችና ጨፈራዎች በመጫወት ያሳያሉ፣<br>• ባህላዊ ጨዋታዎችንና ጭፈራን ከሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በማቀናጀት ይጫወታሉ፣ | **2.1 ባህላዊ ጨዋታዎችና ቅርሶች**<br>2.1.1 የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች<br>*(6 ክፍለ ጊዜ)* | • የልጆች ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• ስለልጆች ባህላዊ ጨዋታዎች አይነት፣ ምንነትና የመጫወቻ ጊዜ ማስረዳት፣<br>• ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሎ የተለያዩ ጨዋታዎችን ተለማምደው ለተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ /በፍላጐት ለሚያቀርቡ ተማሪዎች በቅድሚያ እድል መስጠት/ |
| • ከ3-4 የሚደርሱ የብሔር/ብሔረሰብ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፣ | 2.1.2የብሔር/ብሔረሰብ ጨዋታዎች<br>*(5 ክፍለ ጊዜ)* | • በአካባቢያቸው የሚዘወተሩትን የብሔር ብሔረሰብ ጨዋታዎችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን በመምረጥ በቡድን እንዲጫወቷቸው ማድረግ፣<br>• በቡድን የተለማመዱዋቸውን ለክፍሉ ተማሪዎች አንዲያሳዩና አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ፣<br>• ስለባህላዊ ጨዋታዎች ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፣ |
| • ከ2-3 የሚደርሱ የባህልና ቅርስ ውጤቶችን በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ፣ | 2.1.3ንድፍና ቀለም ቅብ *(4 ክፍለ ጊዜ)* | • የባህልና ቅርስ ውጤቶችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• የባህልና ቅርስ ውጤቶችን በንድፍና ቀለምቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የሠሩትን ሥራዎች ለክፍሉ ተማሪዎች በማሳየት አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ፣ |
| • ባህላዊ የስፖርት መሣሪያዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ባህላዊ የስፖርት መሣሪያዎችን በመጠቀም ይጫወታሉ፣<br><br>• ባህላዊ ስፖርታዊ ጨዋታዎችን | 2.1.4ባህላዊ የስፖርት መሣሪያዎች<br>*(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>• ጨዋታ<br>• ንድፍና ቀለም ቅብ | • ባህላዊና የስፖርት መሣሪያዎችን አይነትና አጨዋወት እንዲዘረዝሩና እንዲገልጹ እድል መስጠት፣<br>• የባህላዊ የስፖርት መሣሪያዎችን ተጠቅመው እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣<br>• በሚጫወቱበት ጊዜ አጨዋወታቸውን በማየት እንስፈላጊነቱ እርምት መስጠት፣ ማበረታታት፣<br>• የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| በንድፍና ቀለም ቅብ ይሠራሉ፣<br>• ባህላዊ የስፖርት መሣሪያዎችን በንድፍና ቀለም ቅብ ይሠራሉ፣ | | • ከዘረዘሯቸው ባህላዊ ጨዋታዎች ውስጥ የወደዱትን በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የተለያዩ የባህላዊ ስፖርትና ሙዚቃ መሣሪያዎችን በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • ከባህላዊ ቅርሶች አጠባበቅ ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣ | 2.1.5የባህላዊ ቅርሶች አጠባበቅ /መዝሙር/ (4 ክፍለ ጊዜ) | • ባህላዊ ቅርሶችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• የዘረዘሯቸውን የባህላዊ ቅርሶችን በመዝሙር መልክ እንዲገልጹ/እንዲዘምሩ ማድረግ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- የንድፍና ቀለም ቅብ መሣሪያዎች/እርሳስ፣ ላጲስ፣ ከተር፣ ውሃ ቀለም፣ ብሩሽ፣ ከለር፣ ክራዮን፣
- ባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች /ከበሮ፣ ዋሽንት፣ ገበጣ፣ ወዘተ..
- በአካባቢው የሚገኙ ባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች
- ባህላዊ የስፖርት መሣሪያም/ገበጣ......../

## ክትትልና ግምገማ፡-

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ቅርጽ፣ ቀለምና ውበትን መረዳታቸውን የሠሩትን ሥራዎች በመገምገም ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ ጨዋታዎችንና ዘፈኖችን መጫወት መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የሙዚቃና ስፖርት ባህላዊ መሣሪያዎችን መጠቀም መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ ጨዋታዎችን በንድፍና ቀለም ቅብ መሥራት መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ከባህላዊ ቅርሶች አጠባበቅ ጋር የተያያዙ መዘመር መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ምዕራፍ ሦስት፡- ጥንቃቄና ደህንነት *(14 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- የአካባቢያቸውን ጽዳትና ውበት ጠቀሜታ በመገንዘብ ተገቢውን እንክብካቤ የማድረግ ክህሎት ያሳያሉ፣
- የአደጋን አስከፊነት ተገንዝበው ራሳቸውን ከአደጋ ይጠብቃሉ፣
- የኤች አይቪ ኤድስን መከሰቻ መንገዶችን በመረዳት ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋሉ፣
- ከጥንቃቄና ደህንነት ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን በሥዕል በመዝሙርና በእንቅስቃሴ ይገልፃሉ፣

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• የንጽህናን ጠቀሜታ በመረዳት ት/ቤታቸውን ያፀዳሉ/ያስውባሉ፣<br>• የት/ቤትን ጽዳት በተመለከተ መዝሙር ይዘምራሉ፣<br>• የት/ቤትን ጽዳት በተመለከተ በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ፣ | **3.1 የት/ቤትን ድህንነት መጠበቅና በዕፅዋት ማስዋብ** *(6 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.1.1 መዝሙር<br>3.1.2 ንድፍና ቀለም ቅብ | • የት/ቤት ደህንነት መጠበቅና በዕጽዋት ማስዋብ ምን ማለት እንደሆነና ጠቀሜታውን እንዲገልጹ እድል በመስጠት ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፣<br>• ለት/ቤት ጽዳትና በዕጽዋት ማስዋብ አስፈላጊ መሣሪያዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣<br>• የት/ቤታቸውን ቅጥር ግቢ በዕጽዋት እንዲያስውቡና እንዲያፀዱ ማድረግ፣<br>• ከት/ቤታቸው ደህንነት አጠባበቅና ማስዋብ ጋር የተያያዘ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• በት/ቤት ደህንነትና አጠባበቅ እንዲሁም በዕጽዋት ማስዋብ ያደረጉትን ተግባራዊ ክንዋኔ ተመርኩዞ በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችንና ነገሮችን ይዘረዝራሉ፣<br>• አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮችን ምክንያትና መወሰድ ያለበትን ጥንቃቄ በመዝሙር፣ በእንቅስቃሴና በንድፍ ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራቶች ምልክትና ሕጐቹን በተግባር ያሳያሉ፣<br>• ስለመንገድ ደህንነት የሚገልጹ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፣ | **3.2 የመንገድ ድህንነት***(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.2.1 የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራቶች ምልክትና ጠቀሜታ<br>3.2.2 መዝሙር<br>3.2.3 ጨዋታ<br>3.2.4 ንድፍና ቀለም ቅብ | • አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• ለአደጋ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን፣ መንስኤያቸውን እና መፍትሔያቸውን በቡድን ከፋፍሎ እንዲወያዩበትና የደረሰቡበትን በየቡድኑ ተወካዮች እንዲቀርቡ ማድረግ፣<br>• የአደጋ መንስኤዎችን/የታሸጉ ምግቦች፣ የኤሌትሪክ ሽቦዎች፣ ምልክት ሳይጠብቁ መሻገር ወዘተ.. እንዴት አደጋ ሊያደርሱ እንደሚችሉ የሚገልጽ በመዝሙር፣ በድራማ፣ በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ስለአደጋ መንስኤዎች እና መወሰድ ያለበትን ጥንቃቄን የሚገልጽ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• ስለአደጋ መንሰኤዎች እና የሚያስከትሉትን ጉዳት እንዲሁም መወሰድ ያለበትን ጥንቃቄ የሚያመለክት ጨዋታ እንዲጫወቱ ማድረግ፣<br>• ጥንቃቄና ደህንነትን በተመለከተ በተለያዩ ተግባራትን |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | በሚሠሩበት ጊዜ ማግኘት ያለባቸውን ግንዛቤ ና ክህሎት ማግኘታቸውን ክትትል በማድረግ ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት፣ |
| • ኤች አይቪ ኤድስ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍባቸውን መንገዶች እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይዘረዝራሉ።<br>• የኤች አይቪ ኤድስ ሕሙማንን ማግለል ተገቢ አለመሆኑን በድራማ መልክ ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• ኤች አይቪ ኤድስን በተመለከተ መዝሙር ይዘምራሉ፣<br>• ለኤች አይቪ ኤድስ የሚደረገውን እንክብካቤ በንድፍና ቀለም ቅብ ይገልሉ፣ | **3.3 ኤች አይቪ ኤድስ** *(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>3.3.1 ለኤች አይቪ ኤድስ/ ሕሙማን እንክብካቤ ማድረግ፣<br>3.3.2 መዝሙር<br>3.3.3 ንድፍና ቀለም | • ተማሪዎች ስለ ኤች አይቪ ኤድስ ምንነትና መተላለፊያ መንገዶችን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• የኤች አይቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችንና ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄ በማብራራት ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣<br>• የኤች አይቪ ኤድስ ሕሙማንን መንከባከብ እንጂ ማግለል እንደማይገባ በማስገንዘብ ከዚህ ጋር የተያየዘ ድራማ ማሠራት፣<br>• ስለኤች አይቪ ኤድስ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• ለኤች አይቪ ኤድስ ህሙማን የሚደረገውን የእንክብካቤ መንገዶች በንድፍና ቀለም ቅብ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ለንድፍና ቀለም ቅብ የሚሆኑ እርሳስ፣ ላጲስ፣ ቀለም፣ ብሩሽ፣ ወረቀት…
- የሙዚቃ መሣሪያዎች ከበሮ፣ ሪትም ስቲክ፣ ዋሽንት….
- ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ሥዕሎች

## ክትትልና ግምገማ፡-

- የት/ቤት ግቢ ጽዳትንና ማስዋብን ጠቀሜታ መገንዘባቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችንና መወሰድ ያለበትን ጥንቃቄ መረዳታቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮችን በንድፍና ቀለም ቅብ፣ መዝሙር መግለጽ መቻላቸውን የሠሩትን በማየት ማረጋገጥ፣
- የኤች አይቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን መገንዘባቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ስለኤች አይቪ ኤድስ መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ለኤች አይቪ ኤድስ ሕሙማን መደረግ የሚገባውን እንክብካቤ በድራማ መልክ መግለጻቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ምዕራፍ አራት፡- የሰውነት ክፍሎች ተግባራት *(54 ክፍለ ጊዜ)*

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- ከእጆችና እግሮች ጋር የተያያዙ መሠረታዊ የእንቅስቃሴ ተግባራትን በተናጠልና በማቀናጀት ሠርተው ያሳያሉ፣

- ከእጆችና እግሮች ክንዋኔዎች ጋር የተያያዙ ጨዋታዎችን በመጫወት ያሳያሉ፣

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፦*<br>• የእጅ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣<br>• ስለእጅ ተግባራት የሚያወሱ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br>• በድንች ሕትመት የተለያዩ ዲዛይኖችን ይሠራሉ፣ | **4.1 በእጅ የሚከናወኑ ተግባራት**<br>*(14 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.1.1 የድንች ሕትመት | • ተማሪዎች ስለ እጅ ተግባራት የሚያውቁትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣<br>• ስለዘረዘሯቸው የእጅ ተግባራት የሚያወሳ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• ስለድንች ሕትመት አሠራር የሚያውቁትን እንዲገልጹ እድል መስጠት፣<br>• የድንች ሕትመት አሠራርን እና አስፈላጊ መሣሪያዎችን ዘርዝሮ ማስረዳት፣<br>• የድንች ሕትመትን መሥሪያ መሣሪያዎች እንዲያዘጋጁ በማድረግ የተለያዩ ቀላል ዲዛይኖችን ነድፈው በመቅርጽ እንዲያትሙ ማድረግ፣ |
| • የግልቢያ ምትን ከጭብጨባና ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ይጫወታሉ ፣<br>• የግልቢያ ምት እንቅስቃሴን በንድፍና በቀለም ቅብ ይሠራሉ፣ | **4.2 እጅና እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራት** *(23 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.2.1 የግልቢያ ምት | • እጅና  እግርን በማቀናጀት የሚሠሩ ተግባራትን እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• እጅና እግርን በማቀናጀት የግልቢያ ምትን እንዴት እንደሚጫወቱ ማሳየት፣ የተወሰኑ ተማሪዎች የግልቢያ ምትን ሲያጨበጭቡ ሌሎቹ ደግሞ ምቱን ተከትለው እንዲጋልቡ ማድረግ፣ |
| • ኳስ ወርውረው በማጨብጨብ ይቀልባሉ፣<br>• እንቅስቃሴዎቹን በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ይገልፃሉ፣ | 4.2.2 ኳስ ወርውሮ ማጨብጨብና መቅለብ | • ኳስ ወርውሮ የመቅለብን ዘዴ እንዲገልጹና በተግባርም እንዲያሳዩ እድል መስጠት፣<br>• ኳስን ወርውሮ በማጨብጨብ የመቅለብን ክህሎት በገለፃና በተግባር ማሣየት፣<br>• ኳስን ወርውሮ በማጨብጨብ መቅለብን ከምት የሙዚቃ መሣሪያ ጋር በማቀናጀት እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • የገመድ ዝላይ በተሻለ ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• የገመድ ዝላይ እንቅስቃሴን በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ፣ | 4.2.3 በቡድን የገመድ ዝላይ | • በቡድን የገመድ ዝላይን እንዴት መሥራት እንዳለባቸው በማስረዳት እንዲጀምሩ ማድረግ፣<br>• የዝላዩን እንቅስቃሴ ፍጥነት እየጨመሩ እንዲጫወቱ ማድረግ፣<br>• የተሻለውን ቡድን መርጦ ለሌሎች እንዲያሳዩ በማድረግ የውድድር ስሜትን ፈጥሮ በተሻለ አፈጻጸም እንዲሠሩ ማድረግ፣ |
| • በሞዛይክ የተለያዩ ዲዛይኖችን ይሠራሉ፣ | 4.2.4. ሞዛይክ | • ስለሞዛይክ ምንነት፣ መሥሪያ መሣሪያዎች እና አሠራሩን እንዲገልጹ መጠየቅ፣<br>• የተለያዩ ነገሮችን በፍላጐታቸው ነድፈው በሞዛይክ እንዲሠሩ ማድረግ፣ |

| *አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| • መራመድና መፈናጠርን እንቅስቃሴ በተሻለ ሰርተው ያሳያሉ፣ | 4.2.5 መራመድና መፈናጠር | • በ3ኛ ክፍል የሠሩትን በማስታወስ በዚህ ክፍል በተሻለ ሁኔታ እንደሚሠሩ በመንገር ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ ማስገንዘብ፣<br>• የመራመድና መፈናጠርን ትክክለኛ አሠራር ሰርቶ ማሣየት፣<br>• ተማሪዎቹ ነፃ ሆነው ባዩት መሠረት አስመስለው እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ከተማሪዎቹ መካከል የተሻለ የሠሩትን ለሌሎች እንዲያሣዩ ማድረግ፣<br>• በቦታ ላይ ቆመውና በመንቀሳቀስ ሚዛን መጠበቅን ሠርተው እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ከተማሪዎች መካከል የተሻለ የሠሩትን በመለየት ለሌሎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣ |
| • ሚዛናቸውን የመጠበቅ እንቅስቃሴን ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• በቂጥ በመቀመጥ እግርን ማንሣት በንድፍና ቀለም ቅብ ሠርተው ያሳያሉ<br>• ኳስ ማንጠርን በተሻለ ሁኔታ ሠርተው ያሳያሉ፣<br>• የኳስ ማንጠር እንቅስቃሴን በሥዕል ይገልጻሉ፣ | 4.2.6 ሚዛን መጠበቅ<br>• በቂጥ በመቀመጥ እግርን ማንሣት፣<br><br>4.2.7 ኳስ ማንጠር | • ኳስ እንዴት እንደሚነጥር መጠየቅና ከምላሻቸው በመነሳት ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣<br>• ኳስን እንዴት እንደሚያነጥሩ በማሣየት ባዩት መሠረት እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• የተሻለ የሠሩትን በመለየት ለሌሎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣ |
| • የተያዩ ቀላል ሪትምን በመጠቀም ጡብ ጡብንና የግልቢያ ምትን በተለያየ ፍጥነት በመጫወት ያሳያሉ፣<br>• ከሙዚቃ ምት ጋር ነፃ እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት ይሠራሉ፣<br>• እንቅስቃሴዎቹን በራሳቸው መንገድ በንድፍ ቀለም ቅብ ይገልጻሉ፣ | **4.3 በሙዚቃ ሪትሚካዊ እንቅስቃሴ**<br>*(17 ክፍለ ጊዜ)*<br>4.3.1 በሙዚቃ ምት ነፃ እንቀስቃሴዎች | • በዚህ ክፍል ደረጃ የጡብ ጡብና የግልቢያ ምት በማፋጠንና ዝግ በማድረግ ተማሪዎቹ ለሚሰሙት ሪትም ተስማሚውን እንቅስቃሴ እንዲጫወቱ በማድረግ ማለማመድ፣<br>• በሙዚቃ ነፃ እንቅስቃሴዎችን ለማለማመድ የብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃ ማሰማትና ተማሪዎች በስርዓት ሆነው እንቅስቃሴውን ከሙዚቃው ጋር አዋህደው እንዲጫወቱ ማድረግ፣<br><br>• በአካባቢው የታወቀ የባህል ሙዚቃ ዜማ በማሰማት ዜማውን በጭብጨባና በተለያዩ የምት መሣሪያዎች ማጀብ እንዲሁም ሙዚቃውን ከነፃ እንቅስቃሴ ጋር በማሰማማት እንደለማመዱት ማበረታታት፣<br>• የታዋቂ ዘፋኞችን ዘፈን አስመስለው እንዲዘፍኑ |

| አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | በጭብጨባና በልዩ ልዩ የሙዚቃ የምት መሣሪያዎች በማጀብ ተስማሚ ነፃ እንቅስቃሴዎች በመሥራት እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>• ከተቻለ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃ በማሰማት ወይም የተለያዩ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ፈጣንና ዝግ ያለ የሙዚቃ ምት በማስማት ተማሪዎች ነፃ ሆነውና ከሚሰሙት የሙዚቃ ምት ጋር ወይም ሙዚቃ ጋር አስማምተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ፣ |

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ቀለም፣ ከተር፣ ድንች፣ የተለያዩ ቀለማት፣ ጠጠር፣ ጥራጥሬ፣ አሸዋ ወዘተ…
- ከበሮ፣ ሪትምስቲክ
- ገመድ፣ ኳስ

## ክትትልና ግምገማ፡-

- የሰውነት ክፍሎቻቸውን በሚገባ ማንቀሳቀስ መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- መሠረታዊ ክህሎት ለምሳሌ ኳስ መወርወር፣ ኳስ ማንጠር ወዘተ… እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው ማወቃቸውን በምልከታና በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፣
- በጨዋታዎች ላይ በንቃት መሣተፋቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ከተለያዩ ተግባራት ጋር የሚሄዱ መዝሙሮችን ከእንቀስቃሴዎች ጋር አቀናጅተው መጫወታቸውን /መዘመራቸውን በምልከታና በማዳመጥ ማረጋገጥ፣
- የመፈናጠርና የመራመድን፣ ሚዛንን የመጠበቅ እንቅስቃሴን፣ ኳስ የማንጠርንና ወርውሮ በማጨብጨብ የመቅለብን እና የገመድ ዝላይ ተግባራትን በተገቢው መንገድ መተግበር መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- በሞዝይክ እና በህትመት የተለያዩ ዲዛይኖችን መሥራት መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ፣